
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ለማቋቋምና ለማጠናከር የተደረገ የአራት ዓመት ጥረትና ውጤት

(ከ፲፱፻፸፭ - ፲፱፻፸፱ ዓ.ም)



ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም

አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org

4/2/1980

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ለማቋቋምና ለማጠናከር የተደረገ የአራት ዓመት ጥረትና ውጤት

(ከ፲፱፻፸፭ - ፲፱፻፸፱ ዓ.ም)

www.ethiopianorthodox.org

## ማ ው ጫ


| ተራ ቍጥር | አ ር እ ስ ት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | መ ግ ቢ ያ | ፭ |
| | ክፍል ፩ | |
| ፪ | የተሻሻለው ቃለ ዓዋዲ | ፮ |
| | ክፍል ፪ | |
| ፫ | በተሻሻለው ቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት ሰበካ ጉባኤን ለማቋቋም. የተደረገ ሀገር አቀፍ ጥረት | ፯ |
| | ክፍል ፫ | |
| ፬ | የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ምሥረታ | ፱ |
| ፭ | የ፲፱፻፸፭ ዓ/ም ሪፖርቶችን በዝርዝር የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ሠንጠረዦች | ፲ |
| ፮ | የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ | ፲፫ |
| ፯ | የ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ሪፖርቶችን በዝርዝር የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ሠንጠረዦች | ፲፬ |
| ፰ | የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባ | ፲፱ |
| | የ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ሪፖርቶችን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ሠንጠረዦች | ፳ |
| ፱ | የመንበረ ፓትርያክ አጠቃላይ ሰበካ መንበፈሳዊ ጉባኤ አራተኛ መደበኛ ስብሰባ | ፳፭ |
| ፲ | የ፲፱፻፸፰ ዓ/ም ሪፖርቶችን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ሠንጠረዦች | ፳፰ |
| | ክፍል ፬ | |
| ፲፩ | የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሥራ ዕቅድና አፈጻጸም | ፴ |
| ፲፪ | የ፬ቱን ዓመት ( ፲፱፻፸፭—፲፱፻፸፰ ዓ/ም) የሥራ ውጤት በማነጻፀር የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎች (ግራፎች) | ፴፫ |
| ፲፫ | ክፍል ፭ | |
| ፲፬ | ሰበካ ጉባኤን ለማደራጀትና ለማጠናከር በየሥራ ዘርፉ የተደረገ አጠቃላይ ጥረት | ፴፯ |
| | ክፍል ፮ | |
| ፲፭ | የወደፊት የሥራ ዕቅዶች | ፴፰ |
| ፲፮ | ማጠቃለያ | ፴፱ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# መ ግ ቢ ያ

በዘመነ ኦሪት መንፈሳዊ አገልግሎት ይካሄድ የነበረው ምእመናኑ ከገንዘባቸው ከአዝመራቸውና ከጥሪታቸው በሚሰጡት አሥራት በኵራት ነበር።

አሥራት ማለት ከማንኛውም ገቢ ከአሥር አንድ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጥ ክፍያ ማለት ነው ። ይህም የእያንዳንዱ ምእመን ሃይማኖታዊ ውዴታና ግዴታ ነበር ።

ሕገ ኦሪት ከመሰጠቱ በፊት አብርሃም ለእግዚአብሔር ካህን ለመልከ ጼዴቅ ከገንዘቡ ፥ ከእህሉና ከእንስሳቱ ሁሉ ከአሥር አንድ እንደሰጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል ። (ዘፍጥ ፥ ፲፬፡፲፯—፳፬) ።

ክርእሳነ አበው አንዱ የሆነው ያዕቆብም «እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን በምሄድባትም በዚህች መንገድ ቢጠብቀኝ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ ለሐውልት የተከልሁት ይህ ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል ፤ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር አንድ እሰጣለሁ» ብሎ በተሳለው መሠረት ሲፈጽም ኑሮአል (ዘፍጥ፡ ፳፰፡ ፲፰—፳፪) ።

ሕገ ኦሪት ከተሰጠበትና የሌዊ ልጆች ለክህነት ሥራ ከተመረጡ ወዲህም እግዚአብሔር ለሊቀ ካህናቱ ለአሮን «የሌዊ ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ስለሚሰጡ የእስራኤልን አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቼሃለሁ» ሲል እንደ ተናገረው ተጽፏል (ዘኁልቍ ፲፰ ፥ ፳፩—፴፪) ።

እግዚአብሔር አምላክ ሌሎች ፍጥረታትን ለይኩን ብሎ ሲፈጥራቸው ሰውን ግን በመልኩና በምሳሌው መፍጠሩ ራሱም ተከብሮ ፈጣሪውንም አክብሮ እንዲኖር ነበር ። በኋላም የሰው ልጅ በምክረ ከይሲ ተሳስቶ በሠራው ኃጢአት ምክንያት ከተድላ ገነት ስለወጣ እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ በሥጋ ሰብእ ተገልጾ በደሙ ዋጅቶ እንደገና ወደቀደመ መንበሩ ወደገነት እንዲመለስ ማድረጉ አምላኩን እግዚአብሔርን እየቀደሰና እያወደሰ በተድላ በደስታ እንዲኖር ነው ።

ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ሳለ ክርስቲያናዊ ሕይወቱ በምግባርና በፍሬ ትሩፋት መበልጸግ ይኖርበታል ። የአንድ ምእመን የእምነቱ መግለጫ ስነ ምግባርና ልዩ ልዩ ትሩፋት ነው ። ከሃይማኖታዊ ምግባሩ አንዱም የአሥራት በኵራት አስተዋጽኦ ነው ።

ዘመነ ኦሪት አልፎ ዘመነ ሐዲስ በተተካበት ወቅት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያን ስለግብር አከፋፈል ሊፈታተኑት በቀረቡ ጊዜ «የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሳርን ለቄሳር» ሲል የተናገረው ቃል ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ ሲፈጸም የነበረውን የአሥራት አስተዋጽኦ አስፈላጊነት የሚያረጋግጥ ነው(ማቴ ፥ ምዕ ፥ ፳፪ ፥ ፳፩) ።

ሐዋርያው ጳውሎስም በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክቱ «ይህንም እላለሁ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ይሰበስባል» - - - - - «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም» ሲል ያስገነዘበው ቃል እያንዳንዱ ምእመን ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን አስተዋጽኦ መለገስ እንዳለበት ያረጋግጣል (2ኛ ቆሮ ፱ ፥ ፮—፯) ።

ኢትዮጵያውያን ምእመናን ሕገ ኦሪት ወደ ሀገራችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የኦሪቱን ሕግ በመከተል የሚገባውን አሥራት በኵራት ለቤተ እግዚአብሔር ሲያቀርቡ እንደኖሩ አሁንም በተግባር የሚታይ ሐቅ ነው ።

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት በይበልጥ የተሟላ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ «ቃለ ዓዋዲ» በሚል ርእስ የተዘጋጀ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ በማውጣት ከጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል አደረገ ።

በዚሁ ደንብ መሠረትም በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክልል የሚገኙ ምእመናንን በሰበካ ጉባኤ ለማደራጀት በዚያ ጊዜ የተደረገው ሙከራ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም ።

ሆኖም በ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ተዘጋጅቶ የወጣው የቃለ ዓዋዲ ደንብ ከጊዜያችን የአሠራር ስልት ጋር የማይጣመድና ሁሉንም ምእመናን የማያጠቃልል ስለሆነ የተሻሻለው የቃለ ዓዋዲ ደንብ መውጣት እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ። በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀመንበርነት የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ለቃለ ዓዋዲው ደንብ መሻሻል ቅድሚያ የሰጠውም በዚህ ምክንያት ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፩

# የተሻሻለው ቃለ ዓዋዲ

፩/ ቤተ ክርስቲያን በምእመናን አንድነት መደራጀቷ ፤ በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደርም መመራቷ ከጥንት ጀምሮ ያለ እንጂ አዲስ አለመ ሆኑና አመራሯና አስተዳደርዋም በኢየሩሳሌም በተ ደረገው በሐዋርያት ጉባኤ ተመክሮና ተወስኖ በተ ላለፈው ሕግና ሥርዓት በማኅበረ ምእመናኑ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ በተመረጡ ቅዱስ መንፈስ ባደረ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋር ።

ባቸው ኃላፊዎች ሥራ አስፈጻሚነት ይካሄድ እንደ ነበር (ግብረ ሐዋ ምዕ ፮ ፣ ፩—፮) ሀብቷና ንብ ረቷም ከምእመናን በአስተዋጽኦ ተሰብስቦ ለአገል ጋዮቿ መተዳደሪያ ፣ ለሐዋርያዊ ሥራ ማስኬጃና ለችግረኞች መርጃ እንዲውል ይደረግ እንደ ነበር (ግብረ ሐዋ ምዕ ፣ ፬፣፴፪ ምዕ ፭፣፲፩ ። ፩ኛ ቆሮ ፣ ምዕ ፲፮ ፣ ፮—፲፩) በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ተመልክ ቷል ።

፪/ በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ዓላማና ተግ ባርም ከዚህ የልለየ መሆን ስለማይኖርበት ፤

፪.፩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮዎች ምእመናን በሃይማኖት እንዲ ፀኑ ፤ በመንፈሳዊ ዕውቀት እንዲጐለምሱና በስነ ምግባር እንዲታነጹ ፤

፪.፪ ስብከተ ወንጌል እንዲጠናከር ፤

፪.፫ ጥንታዊውና ነባሩ የቤተ ክርስቲያን መን ፈሳዊ ትምህርት መሠረታዊ ይዘቱ ሳይፋ ለስ በየደረጃው እንዲጠናከርና የቤተ ክር ስቲያን አዕማድ ለሆኑት ሊቃውንትና መም ህራን ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግ ፣

፪.፬ ካህናት ለምእመናን የሚያበረክቱት መን ፈሳዊ አገልግሎትና ምእመናንም ለቤተ ክር ስቲያን ሊያደርጉት የሚገባቸው አስተዋ ጽኦ የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ ፣

፪.፭ ከምእመናን በሚገኘው አስተዋጽኦ የካህ ናትን ኑሮ ለማሻሻል ፣

፪.፮ እያንዳንዱ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የወደ ፊቱን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ተተ ኪዎች የማዘጋጀት ኃላፊነት ስለአለበት የሰ ንበት ትምህርት ቤትን በእያንዳንዱ አጥቢ ቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋምና ለማጠና ከር ፤

፪.፯ በሰበካ ጉባኤያት አማካይነት ተግባረዕድን ለማስፋፋትና በውጤቱም የተሟላ መንፈ ሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለማበርከት የሚረዳ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ፤

፪.፰ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን ከጥንት ጀምሮ ምስካየ ኅዙናን መጽንኤ ድኩማን እንደመሆንዋ አሁንም በእያንዳንዱ የአጥቢያ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እጓለ ማውታ ሕፃናት በእንክብካቤ የሚ ያድጉበት ፣ ሽማግሌዎች የሚጦሩበትና ችግ ረኞች የሚረዱበት የምግባረ ሠናይ ድር ጅት እንዲኖር ፤

፪.፱ የቤተ ክርስቲያን ገንዘብና ንብረት እንዲ ሁም ታሪካዊነትና ጥንታዊነት ያላቸው ቅር ሶች በጥንቃቄ እንዲጠበቁና አያያዛቸውም ዘመናዊ እቅድ እንዲኖረው ለማድረግ ፤

፪.፲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን አገልጋዮች ካህናትና ሠራተኞች ሁሉ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ሠራ ተኛ መብታቸው የተጠበቀ ይሆን ዘንድ የጡረታ አስተዋጽኦ መክፈልና የጡረታ አበል ማግኘት እንዲችሉ ፤

፪.፲፩ በአጠቃላይ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ወረዳ ፣ ከወረዳ እስከ አውራጃ፣ ከአውራጃ እስከ ሀገረ ስብከት ፣ ከሀገረ ስብከት እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ድረስ ሰበካ ጉባኤን ደረጃ በደረጃ በማቋቋም የቤ ተ ክርስቲያንን አስተዳደር በማዕከላዊ አመ ራር ለማጠናከር ይቻል ዘንድ ቅዱስ ሲኖዶስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፲፰ እና ፫፻ ፺፱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተሰጠው መብት መሠረት የተሻሻለውን የቃለ ዓዋዲ ደንብ አውጥቷል ።

## ክፍል ፪

# በተሻሻለው የቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት ሰበካ ጉባኤን ለማቋቋም የተደረገ ሀገር አቀፍ ጥረት፣

፩/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሻሻለውን ቃለ ዓዋዲ ደንብ አውጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል ከአደረገ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር ደን ቡን በትክክል ለመፈጸምና ለማስፈጸም የተቻ ለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ስለነበር ለቤተ ክር ስቲያናችን ዕድገትና ጥንካሬ አስተማማኝ የሆ ነውን ይህን የቃለ ዓዋዲ ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በቅድሚያ የደንቡ ዓላማና ይዘት ለሁሉም ግልጽ ሁኖ እንዲገኝ ከዚያም ምእመናንን በየደረጃው በሰበካ ጉባ ኤያት ለማደራጀት ውጤታማ የሆኑ የት ምህርተ? ስቀሳ ሰሚናሮች በየጊዜው ተካሂዶአል ፤ የውሳኔ ማስፈጸሚያ መመሪያዎችና የት እዛዝ ደብዳቤዎችም በየጊዜው ተላልፈዋል።

፪/ ተሻሽሎ በወጣው የቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠ ረት ሰበካ ጉባኤን ለማቋቋምና ለማጠና ከር በየሀገረ ስብከቱ የተካሄዱ የጥናትና ቅስ ቀሳ ሰሚናሮችና የተሳታፊዎች ብዛት

፪/፩ ከሚያዝያ ፳፰ እስከ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ም በከፋና በኢሉባቦር ፩፻ ተሳታፊዎች

፪/፪ ከሐምሌ ፩ እስከ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፸ዓ/ም በጐጃምና በጎንደር ፪፻፲፯ ተሳታፊዎች





www.ethiopianorthodox.org

፪·፫ ከኅዳር ፲ እስከ ታህሣሥ ፪ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በወለጋና በአርሲ ፩፻፱ ተሳታፊዎች

፪·፬ ከጥር ፳ እስከ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በትግራይና በወሎ ፪፻፺ ተሳታፊዎች

፪·፭ ከግንቦት ፬ እስከ ግንቦት ፳፮ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በጋሞጎፋና በባሌ ፩፻፳፰ ተሳታፊዎች

፪·፮ ከነሐሴ ፲፰ እስከ ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በአርሲና በአዲስ አበባ ፫፻፳፱ ተሳታፊዎች

፪·፯ ከጥር ፲፩ እስከ ፳፬ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም በሐረርጌ ፩፻፳፬ ተሳታፊዎች

፪·፰ ከነሐሴ ፳ እስከ ፳፭ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም በኤርትራ ፩፻፺ ተሳታፊዎች

በአሥራ አራቱ አህጉረ ስብከት በጠቅላላ ፩ሺህ፫፻፺፱ ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን በእነዚህ ሰሚናሮች የየሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች ፣ የአውራጃና ወረዳ ሊቃነ ካህናት ፣ ሰባክያነ ወንጌል ፣ የምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች ተካፋዮች ሁነዋል ።

፫/ ከኅዳር ፲፭ እስከ ታህሣሥ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፫ዓ/ም ድረስ ስለሰበካ ጉባኤ ዓላማና ተግባር ለየመምሪያው ኃላፊዎች ፣ ለየሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች ፣ ለካህናትና ምእመናን ፣ ለሰንበት ት/ቤት ተወካዮችና ለሰባክያነ ወንጌል በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ አገር አቀፍ ሰሚናር ተካሂዷል ።

፬/ ለሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የሰበካ ጉባኤን ዓላማና ተግባር ለማስረዳት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ የምእመናኑ መምህራን ንስሐ የሆኑትን ካህናት ማሰልጠን አስፈላጊ በመሆኑ ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ለተውጣጡ ፩፻፺ ካህናት ከግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ምጀምሮ ለሦስት ወራት ያህል በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ የሰበካ ጉባኤ ማቋቋሚያና ማጠናከሪያ ኮርስ ተደርጓል ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በየሀገረ ስብከቱና በመንበረ ፓትርያርክ ደረጃ የተካሄዱት የጥናት ጉባኤያት በሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ አሳሳቢነትና አስፈጻሚነት የተካሄዱ ሲሆን አሁን ቤተ ክርስቲያን ለምትመራበት የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ አመሠራረት ተገቢውን አስተዋጽኦ አበርክቷል።



## ክፍል ፫


# የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ

፩/ የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ምሥረታ ፣

፩/፩ በቃለ ዓዋዲው ደንብ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል ተራ ከሀ—ሐ በተመለከተው መሠረት የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት ፣ የካህናትና ምእመናን ተወካዮችና የሰንበት ትምህርት ቤት ተጠሪዎች በተገኙበት ከግንቦት ፳፬—፳፰ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ/ም በተካሄደው አገር አቀፍ ስብሰባ የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተመሠረተ ።

ጉባኤው የተመራው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ መንበርነት ሲሆን ፕሮግራሙ የተካሄደው በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ነበር ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የመንበረ ፓትርያርክ አንደኛ መደበኛ ስብሰባን በጸሎት በከፈቱበት ወቅት





www.ethiopianorthodox.org

ለዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊ ጉባኤ በ፲፰ ቱም አህጉረ ስብከት በየዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ሥራዎችን የሚያመለክቱ ሪፖርቶች ቀርበዋል ።

፩ · ፱ በሪፖርቶቹ የተገለጹት ዋና ዋና ነጥቦች በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ባሉት አውራጃዎችና ወረዳዎች ሰበካ ጉባኤን ለማደራጀትና ለማጠናከር ፤ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና መንፈሳዊ አገልግሎትን ለምእመናን ለማዳረስ ፣ ምእመናንን በሰበካ ጉባኤ አባልነት ለመመዝገብና ተገቢውን አስተዋጽኦ ለማሰባሰብ እንዲሁም የመሳሰሉትን ዓበይት ተግባሮች ለማከናወን የተደረገውን ጥረት የሚጠቁሙ ነበሩ ።

በጊዜው በተደረገው ጥረት በሰበካ ጉባኤ የተደራጁ አብያተ ክርስቲያናትና ምእመናን ብዛት እንዲሁም ከምእመናን የተገኘው ገቢ በሚከተለው ሥዕላዊ መግለጫና አኀዛዊ ሠንጠረዥ ተመልክቶአል ።

**እስከ ፲፱፻፸፰ ዓ. ም. የተቋቋሙትን የሰበካ ጉባኤያትንና የሰንበት ት/ቤቶችን እንዲሁም የተመዘገቡ ምእመናን ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| ተ. ቁ. | ሀገረ ስብከት | የተቋቋሙ የሰበካ ጉባኤያት ብዛት | የሰንበት ት/ ቤቶች ብዛት | የተመዘገቡ ምእ መናን በጢስ | በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ ካህናትና ምእ መናን ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 99 | 32 | 43960 | 122977 |
| 2 | ሲዳሞ | 183 | 80 | 72618 | 1658525 |
| 3 | ሸዋ | 2817 | 137 | 707136 | 2849000 |
| 4 | ባሌ | 89 | 12 | 22658 | 127558 |
| 5 | ትግራይ | 87 | 48 | 32552 | 155207 |
| 6 | አርሲ | 262 | 7 | 91939 | 383526 |
| 7 | አዲስ አበባ | 42 | 41 | 96950 | 506800 |
| 8 | ኢሉባቦር | 166 | 28 | 52114 | 194058 |
| 9 | ኤርትራ | 64 | 26 | 50503 | 170575 |
| 10 | ከፋ | 233 | 25 | 63624 | 290265 |
| 11 | ወለጋ | 668 | 22 | 174776 | 644145 |
| 12 | ወሎ | 1549 | 26 | 432775 | 965915 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 115 | 23 | 35688 | 127398 |
| 14 | ጎንደር | 2480 | 2 | 322024 | 1178517 |
| 15 | ጐጃም | 2745 | 432 | 424279 | 2150728 |
| | ጠቅላላ ድምር | 11599 | 941 | 2623596 | 11525195 |



**በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ የካህናትን ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

( ፲፱፻፸፰ ዓ.ም )

| ተ. ቁ. | ሀገረ ስብከት | ቀሳውስት | ዲያቆናት | መዘምራን | ልዩ ልዩ ሠራተኞች | የአገልጋዮች ብዛት ጠ/ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 352 | 399 | 291 | 233 | 1275 |
| 2 | ሲዳሞ | 431 | 526 | 237 | 435 | 1629 |
| 3 | ሸዋ | 13647 | 14062 | 11905 | 7794 | 47408 |
| 4 | ባሌ | 244 | 288 | 162 | 186 | 880 |
| 5 | ትግራይ | 1777 | 1637 | 273 | 218 | 3905 |
| 6 | አርሲ | 1296 | 1261 | 759 | 581 | 3897 |
| 7 | አዲስ አበባ | 475 | 386 | 492 | 575 | 1928 |
| 8 | ኢሉባቦር | 331 | 263 | 267 | 197 | 1058 |
| 9 | ኤርትራ | 3205 | 2095 | 513 | 365 | 6178 |
| 10 | ከፋ | 582 | 583 | 286 | 549 | 2000 |
| 11 | ወለጋ | 1386 | 1812 | 514 | 718 | 4430 |
| 12 | ወሎ | 10527 | 6122 | 4772 | 3307 | 24728 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 230 | 320 | 140 | 177 | 867 |
| 14 | ጎንደር | 22068 | 16298 | 12486 | 5383 | 56235 |
| 15 | ጐጃም | 23085 | 13056 | 16814 | 7304 | 60259 |
| | ጠቅላላ ድምር | 79636 | 59108 | 49911 | 28022 | 216677 |



www.ethiopianorthodox.org

## በየሀገረ ስብከቱ ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ገቢ የሆነ የሰ/ መ/ ጉ/ ክፍያ ፣ የስእለትና የሙዳየ ምጽዋትና የልዩ ልዩ ገቢዎችን አጠቃሎ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

(፲፱፻፸፭ ዓ/ም)

| ተ. ቊ. | ሀገረስብከት | ከሰ/ መ/ጉ የአባልነት ክፍያ | | ከስእለት ከሙዳየ ምጽዋት ፣ ከልዩ ልዩ ገቢ | | ድ ም ር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 124431 | 75 | 122792 | 65 | 247224 | 40 |
| 2 | ሲዳሞ | 152369 | 15 | 131814 | 47 | 284183 | 62 |
| 3 | ሸዋ | 2990498 | 05 | 294464 | 01 | 3284962 | 06 |
| 4 | ባሌ | 88024 | 50 | 6165 | 85 | 94190 | 35 |
| 5 | ትግራይ | 157064 | 40 | 105930 | 10 | 262994 | 50 |
| 6 | አርሲ | 209174 | 70 | 16957 | 86 | 226132 | 56 |
| 7 | አዲስ አበባ | 551396 | 97 | 2741914 | 38 | 3293311 | 35 |
| 8 | ኢሉባቦር | 62158 | 15 | 33199 | 16 | 95357 | 31 |
| 9 | ኤርትራ | 13653 | 80 | 508313 | 91 | 521967 | 71 |
| 10 | ከፋ | 217970 | 70 | 99833 | 40 | 317804 | 10 |
| 11 | ወለጋ | 192923 | 61 | 82412 | 17 | 275335 | 78 |
| 12 | ወሎ | 723803 | 38 | 362162 | 24 | 1085965 | 62 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 44164 | 56 | 34950 | 09 | 79114 | 65 |
| 14 | ጎንደር | 325864 | 19 | 146252 | 55 | 472116 | 74 |
| 15 | ጐጃም | 2123401 | 80 | 182427 | 80 | 2305829 | 60 |
| | ጠቅላላ ድምር | 7976899 | 71 | 4869590 | 64 | 12,8464,90 | 35 |

፩·፫ ከገንቢ ውይይት በኋላ ዓቢይ ጉባኤው በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፵፮ ከንዑስ ቁጥር ፩—፭ በተመለከተው መሠረት በቅዱስ ሲኖዶስ ተወስኖና ተፈ ቅዶ የሚሰጠውንና በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚተላለፈውን ሕግ ፣ ደንብና መመሪያ ለየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት በወቅቱ እያስተ ላለፈ እንዲፈጽምና እንዲያስፈጽም የሚያ ደርግ ስድስት አባላትን የያዘ የሥራ አስፈ ጻሚ ኮሚቴ መረጠ ።

፩·፬ ከግንቦት ፳፬—፳፰ ቀን ፲፱፻፸፭ዓ/ም የተካ ሄደው የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያ ርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ፣

ሀ/ ስለምእመናን በሰበካ ጉባኤ መደራጀት አስ ፈላጊነት ፣

ለ/ ስለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ፣

ሐ/ ስለካህናት ማሰልጠኛዎች ጥራትና ዕድገት፣

መ/ ስለነባር ሰባክያን የአጫጭር ጊዜ ኮርስ አሰጣጥ ፣



ሠ/ ስለጋዜጦችና መጽሔቶች ስርጭት ፣

ረ/ ስለሰበካ ጉባኤ የገቢ መሰብሰቢያ ሞዴሎች ኅትመት

ሰ/ ስለሰባክያነ ወንጌል ብቃትና ጥራት ፣

ሸ/ ስለማዕከላዊ አመራር መጠናከር ፣

ቀ/ ስለሰበካ ጉባኤ አስተዋጽኦ ግዴታ

በ/ ስለሂሣብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ጥን ቃቄ ፣

ተ/ ስለልማት ሥራዎች መስፋፋት ፣

ቸ/ ስለሰንበት ትምህርት ቤቶች መቋቋምና መ መጠናከር ፣

ኀ/ ስለካህናት የጡረታ አበል አወሳሰን ፣

ነ/ ስለድርብ በዓላት አከባበርና ስለመቃብር ቦታ ፣

ኘ/ ስለአገልጋይ ካህናት መጠን አወሳሰን ፣

አ/ ስለቅርሳቅርስ አጠባበቅና አመዘጋገብ ጥን ቃቄ ፣


ከ/ ስለእጓለ ማውታ ሕፃናት እንክብካቤና በመ ሳሰሉት ዓበይት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ተገቢውን ውሣኔና መመሪያ ሰጥቷል ።

## መንፈሳዊ ጉባኤ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ፥

### ፪/ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ

፪·፩ ሁለተኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀመንበርነት፣ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪ ያጅና የጉባኤው ዋና ጸሐፊ የፕሮግራም መሪ ነት በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሥራ አስፈ ጻሚ ኮሚቴ አዘጋጅነት ከግንቦት ፲፬—፲፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተካሂዷል ። በስ

በቅዱስነታቸው ሊቀመንበርነት የተመራው የመንበረ ፓትርያርክ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ



www.ethiopianorthodox.org

ብሰባውም ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያና የዋና ክፍልኃላፊዎች የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ካህናት ፣ የካህናትና የምእመናን ተወካዮ ችና የሰንበት ት/ቤት ተጠሪዎች በአባል ነት ተገኝተዋል ።

፪.፪ ለዚህ ዓቢይ ጉባኤ የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በቤተ ክርስቲያናችን የሥራ ዘርፎች የተከናወኑ ሥራዎችን ፣ ያልተፈጸሙ ተግባሮችንና ወደፊት የተያዙ እቅዶችን በማስመልከት አጠቃላይ ሪፖርት አሰምተዋል ።

፪.፫ ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት በአንደኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ጉባኤ በተሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሠረት በሥራ የተተረጐሙትንና የወደፊት ዕቅዶችን የሚመለከት በአሐዝና በግራፍ የተደገፈ ሪፖርት ቀርቧል ።

፪.፬ የየሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች (ሊቃነ ካህናት) በሀገረ ስብከታቸው የተሠራውን ሥራና የተያዘውን እቅድ በማገናዘብ በመርሐ ግብሩ መሠረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ሪፖርት አቅርበዋል ።

በሁለተኛው ዓመት በሰበካ ጉባኤ የተከናወነውን የሥራ ውጤት የሚያመለክት፣ ሥዕላዊ መግለጫና አሐዛዊ ሠንጠረዥ በሚከተለው አኳኋን በዝርዝር ተመልክቷል ።

ሰበካ ጉባኤያት የተቋቋመባቸውና ት/ ቤቶች ያሉአቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ

( ፲፱፻፸፯ ዓ/ም )

| ተ ቁ | ሀገረ ስብከት | ሰበካ ጉባኤ የተ ቋቋመባቸው አብ ያተ ክርስቲያናት ብዛት | ቆሚ የቤ/ ክ/ መንፈሳዊ ት/ቤት የአላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | የሰንበት ት/ቤት የአላቸው አብ ያተ ክርስቲ ያናት ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 109 | 23 | 28 |
| 2 | ሲዳሞ | 204 | 26 | 59 |
| 3 | ሸዋ | 2794 | 196 | 87 |
| 4 | ባሌ | 92 | 5 | 14 |
| 5 | ትግራይ | 206 | 95 | 52 |
| 6 | አርሲ | 266 | 8 | 7 |
| 7 | አዲስአበባ | 40 | 37 | 39 |
| 8 | ኢሉባቦር | 165 | 3 | 21 |
| 9 | ኤርትራ | 127 | 140 | 28 |
| 10 | ከፋ | 274 | 7 | 15 |
| 11 | ወለጋ | 686 | 7 | 15 |
| 12 | ወሎ | 1668 | 296 | 116 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 115 | 10 | 25 |
| 14 | ጎንደር | 2790 | 1696 | 1665 |
| 15 | ጐጃም | 2736 | 1863 | 1060 |
| | ድምር | 12272 | 4412 | 3231 |

በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ የካህናትና የምእመናን ብዛት የ፲፱፻፸፯ ዓ/ ም፥

| ተ. ቁ. | የሀገረ ስብከቱ ስም | ቀሳውስት ከነ አስተዳዳሪው | ዲያቆናት | ቋሚ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት መምህራን | መዘምራን | ልዩ ልዩ ሠራተኞች | የአገልጋዮች ብዛት ድምር | በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ ምእመናን ብዛት በጠቅላላ ቤተሰቦቻቸውን ሳይጨምር | የካህናትና የምእመናን ብዛት ከነቤሰቦቻቸው ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 396 | 412 | 26 | 226 | 254 | 1364 | 47105 | 139496 |
| 2 | ሲዳሞ | 465 | 539 | 25 | 207 | 457 | 1533 | 72159 | 221243 |
| 3 | ሸዋ | 13713 | 13305 | 299 | 10919 | 7900 | 16136 | 674461 | 2568224 |
| 4 | ባሌ | 271 | 294 | 8 | 135 | 184 | 941 | 29749 | 109676 |
| 5 | ትግራይ | 5524 | 3826 | 198 | 754 | 317 | 10612 | 47147 | 220110 |
| 6 | አርሲ | 1473 | 1276 | 15 | 722 | 545 | 4027 | 98553 | 424446 |
| 7 | አዲስ አበባ | 488 | 366 | 105 | 435 | 581 | 1974 | 102271 | 506515 |
| 8 | ኢሉባቦር | 408 | 282 | 3 | 234 | 202 | 1130 | 46090 | 173840 |
| 9 | ኤርትራ | 3602 | 1890 | 193 | 492 | 251 | 6296 | 15403 | 52285 |
| 10 | ከፋ | 625 | 580 | 10 | 268 | 532 | 1999 | 68259 | 295581 |
| 11 | ወለጋ | 1431 | 1783 | 10 | 422 | 706 | 4390 | 166930 | 691091 |
| 12 | ወሎ | 10587 | 8178 | 620 | 5059 | 3434 | 62029 | 226260 | 885230 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 233 | 282 | 10 | 147 | 137 | 808 | 41377 | 146214 |
| 14 | ጎንደር | 23826 | 18545 | 2653 | 12687 | 6656 | 60508 | 405701 | 1500284 |
| 15 | ጐጃም | 22673 | 12744 | 3237 | 16072 | 5591 | 59196 | 424285 | 1941467 |
| | ጠ/ ድምር | 85715 | 64302 | 7412 | 48779 | 27747 | 262943 | 2465750 | 9639702 |



www.ethiopianorthodox.org

## በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናት
## የገንዘብ ገቢ መግለጫ ሠንጠረዥ
### ( ፲፱፻፸፯ ዓ/ም )

| ተ.ቁ | ሀገረ ስብከት | ከሰ/ መ/ ጉ/ የአባልነት ክፍያ | | ከስእለትና ከልዩ ልዩ ገቢ | | የገቢ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 193093 | 35 | 156270 | 70 | 349364 | 05 |
| 2 | ሲዳሞ | 170974 | 15 | 180812 | 27 | 351786 | 42 |
| 3 | ሸዋ | 2940991 | 40 | 350641 | 01 | 3291632 | 41 |
| 4 | ባሌ | 118814 | 50 | 16825 | 70 | 135640 | 20 |
| 5 | ትግራይ | 184973 | 45 | 154690 | 31 | 373473 | 72 |
| 6 | አርሲ | 308083 | 75 | 35736 | 18 | 343819 | 93 |
| 7 | አዲስአበባ | 540079 | 72 | 2965255 | 67 | 3505335 | 39 |
| 8 | ኢሉባቦር | 54265 | 65 | 42971 | 40 | 97237 | 05 |
| 9 | ኤርትራ | 73754 | 37 | 528244 | 09 | 601998 | 46 |
| 10 | ከፋ | 195172 | 33 | 142119 | 84 | 337292 | 17 |
| 11 | ወለጋ | 170022 | 25 | 106284 | 05 | 276306 | 30 |
| 12 | ወሎ | 625952 | 71 | 194383 | 13 | 820335 | 84 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 39669 | 32 | 34393 | 24 | 74062 | 56 |
| 14 | ጎንደር | 376507 | 85 | 230790 | 18 | 607298 | 03 |
| 15 | ጐጃም | 2218867 | 62 | 217658 | 67 | 2436526 | 29 |
| | ጠቅላላ ድምር | 8211222 | 42 | 5357076 | 44 | 13568298 | 86 |



## በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናት
## የገንዘብ ወጪ መግለጫ ሠንጠረዥ ፤
### ( ፲፱፻፸፯ ዓ/ም )

| ተ.ቁ. | ሀገረ ብከት | ለወረዳው የተከፈለ 10% | | ለደመወዝ | | ለሥራ ማስኬጃ | | ልዩ ልዩ ወጪ | | የወጪ ጠቅላላ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 34936 | 40 | 213537 | 76 | 16913 | 25 | 19021 | 89 | 284409 | 30 |
| 2 | ሲዳሞ | 35178 | 64 | 205388 | 36 | 22956 | 59 | 47299 | 02 | 310822 | 61 |
| 3 | ሸዋ | 329163 | 24 | 1920187 | 27 | 414638 | 31 | 351720 | 44 | 3015709 | 26 |
| 4 | ባሌ | 13564 | 02 | 86739 | 00 | 9315 | 50 | 8982 | 90 | 118601 | 42 |
| 5 | ትግራይ | 37347 | 37 | 224878 | 20 | 33590 | 43 | 31393 | 19 | 327209 | 19 |
| 6 | አርሲ | 34381 | 99 | 214383 | 25 | 35341 | 76 | 26297 | 22 | 303034 | 22 |
| 7 | አዲስ አበባ | 350533 | 53 | 2308545 | 35 | 239125 | 18 | 765690 | 32 | 3663894 | 38 |
| 8 | ኢሉባቦር | 9723 | 71 | 51369 | 33 | 7071 | 41 | 15893 | 23 | 84057 | 68 |
| 9 | ኤርትራ | 60199 | 84 | 312967 | 10 | 62670 | 45 | 133427 | 40 | 569264 | 79 |
| 10 | ከፋ | 33729 | 22 | 190698 | 20 | 29861 | 59 | 37446 | 04 | 291735 | 05 |
| 11 | ወለጋ | 27630 | 63 | 158053 | 95 | 37246 | 75 | 29766 | 52 | 252697 | 85 |
| 12 | ወሎ | 82033 | 58 | 366637 | 62 | 86364 | 16 | 194918 | 34 | 729953 | 70 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 7406 | 25 | 35360 | 81 | 7604 | 00 | 9178 | 85 | 59549 | 92 |
| 14 | ጎንደር | 60729 | 80 | 172502 | 58 | 89044 | 85 | 142902 | 02 | 472172 | 25 |
| 15 | ጐጃም | 243652 | 63 | 1290137 | 02 | 309044 | 42 | 239371 | 54 | 2082205 | 61 |
| | ድምር | 1360210 | 85 | 7751385 | 80 | 1400788 | 65 | 2053308 | 92 | 12565317 | 23 |



www.ethiopianorthodox.org

| ተ. ቍ. | የሀገረ ስብከቱ ስም | የ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ገቢ ጠቅላላ ድምር | | የ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ወጪ ጠቅላላ ድምር | | የ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ከወጪ ቀሪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 349364 | 05 | 284409 | 30 | 64954 | 75 |
| 2 | ሲዳሞ | 351786 | 42 | 310822 | 61 | 40963 | 81 |
| 3 | ሸዋ | 3291632 | 41 | 3015709 | 26 | 275923 | 15 |
| 4 | ባሌ | 135640 | 20 | 118601 | 42 | 17038 | 78 |
| 5 | ትግራይ | 373473 | 72 | 327209 | 19 | 46264 | 53 |
| 6 | አርሲ | 343819 | 93 | 303034 | 22 | 40785 | 71 |
| 7 | አዲስ አበባ | 3505335 | 39 | 3663894 | 38 | | |
| 8 | ኢሉባቦር | 97237 | 05 | 84057 | 68 | 13179 | 37 |
| 9 | ኤርትራ | 601998 | 46 | 569264 | 79 | 32733 | 67 |
| 10 | ከፋ | 337292 | 17 | 291735 | 05 | 45557 | 12 |
| 11 | ወለጋ | 276306 | 30 | 252697 | 85 | 23608 | 45 |
| 12 | ወሎ | 820335 | 84 | 729953 | 70 | 90382 | 14 |
| 13 | ጋሞጎፋ | 74062 | 56 | 59549 | 92 | 14512 | 64 |
| 14 | ጎንደር | 607298 | 03 | 472172 | 25 | 135118 | 78 |
| 15 | ጐጃም | 2436526 | 29 | 2082205 | 61 | 354320 | 68 |
| | ጠቅላላ ድምር | 13568298 | 86 | 12565317 | 23 | 1195343 | 58 |

፱·፭ ሁለተኛው መደበኛ ጉባኤ በቀረበለት ሪፖርት ላይ ከተወያየ በኋላ ውሳኔና መመሪያ ሰጥቷል ።

፱·፮ <u>በሁለተኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የተላለፈ ውሳኔና ዓመታዊ የሥራ መመሪያ፣</u>

ሀ/ መንፈሳዊው ነባር የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲጠናከር ፣

ለ/ ጉባኤ ዘርግተው ለሚያስተምሩ መምህራን በሀገረ ስብከት ፣ በአውራጃና በወረዳ ደረጃ ደመወዝ እንዲደለደልላቸው ፤ ለደቀ መዛሙርትም እንደ ሰበካ ጉባኤው አቅምና ችሎታ ድጎማ እንዲደረግላቸው ።

ሐ/ ሰበካ ጉባኤያትን ለማጠናከር በመላው አብያተ ክርስቲያናት ሊያገለግል የሚችል የቃለ ዓዋዲ ውስጠ ደንብ እንዲዘጋጅ ፤

መ/ የካህናትን ኑሮ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ከብዛት ይልቅ በጥራት ላይ ትኩረት እንዲደረግ ፤

ሠ/ በ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕ ፲፪ ከቁጥር ፲፬—፳፯ እንደ ተደነገገው የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባላት እንደ አንድ አካል የሚቈጠሩ ስለሆነ ሰባኬ ወንጌል የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት በችግር ምክንያት እንዳይዘጉ ከሀገረ ስብከት እስከ መንበረ ፓትርያርክ ካለው የበላይ አካል ትኩረት እንዲደረግላቸው ።

ረ/ የካህናት በጀት አመዳደብ በሙያና በአገልግሎት ላይ ያተ ኮረ እንዲሆን ፣

ሰ/ በጠረፍ ላሉት ምእመናን ትምህርተ ወን ጌል ለማዳረስ ተዘዋዋሪ ሰባክያን እ... ደቡ እና ለዚሁ ሥራ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ በየደረጃው ከተቋቋሙት ሰበካ ጉባ ኤያት እንዲዋጣ ፤

ሸ/ ለሰባክያነ ወንጌልም ሆነ ለቀሳውስት የሚ ያገለግል የስብከት ዘዴ መጽሐፍ በጥራት እንዲዘጋጅ ፤

ቀ/ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ወደ የሀገረ ስብ ከቱ ከዚያም ወደ አውራጃና ወረዳ ለማስ ራጨት እንዲቻል ከየአንዳንዱ ሀገረ ስብ ከትና ከመንበረ ፓትርያርክ ገቢ ላይ ወር ኃዊና ዓመታዊ በጀት እንዲመደብ ፤

በ/ አዲስ የተዘጋጀው ቅጽ የካህናትንና የምእ መናንን አመዘጋገብ ሲያመለክት የመምህ ራንን ምዝገባ የማይጠቅስ በመሆኑ ተሻሽሎና ተስተካክሎ የመምህራን መመዝገቢያ ኮለም እንዲኖረው ሆኖ እንዲታተም ፤

ተ/ ለቅርሳቅርሶች ጥበቃ አመች በሆነ ቦታ ሙዝየም እንዲሠራና ከየሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በሚሰጥ መመሪያ ተገቢው የአያያዝ ጥንቃቄ እንዲደረግ ፤

ቸ/ በአምስቱም የካህናት ማሰልጠኛ ማዕከላት ከቀለም ትምህርት ሌላ ስለስብከተ ወንጌልና ስለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የሥልጠና ትምህርት በተጨማሪ እንዲሰጥ ፤

ኀ/ በየአብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ የዛፍ ተከላ ተግባር የሚካሄድበት መርሐ ግብር እንዲኖር በመወሰንና በመጀመሪያው ጉባኤ ተወስነው ስላልተፈጸሙት ጉዳዮች አፈጻጸም ተጨማሪ መመሪያ በመስጠት ሁለተኛው ጉባኤ ተፈጽሟል ።

## ፫/ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሦስተኛ መደበኛ ስብሰባ ፤

፫·፩ ከሚያዝያ ፴ እስከ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የተካሄደው ሦስተኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ስብሰባ የተመራው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀመንበርነት ፣ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የቤተክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ የፕሮግራም መሪነት ፣ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መርሐ ግብር አዘጋጅነት ሲሆን በስብሰባው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ፣ የጠቅላይ ቤተክህነት የየመምሪያውና የዋና ክፍል ኃላፊዎች ፣ የየሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጆች (ሊቃነ ካህናት) የየሀገረ ስብከቱ የካህናትና የምእመናን ተወካዮችና የሰንበት ትምህርት ቤት ተጠሪዎች ተገኝተዋል ።



ቅዱስ ፓትርያርኩ ድርቅ ባስከተለው ችግር ምክንያት ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በምልአተ ጉባኤ ውይይት ሲያደርጉ



www.ethiopianorthodox.org

፫ · ፱ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና በአጠቃላይ ጉባኤው ዋና ጸሐፊ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በአንደኛውና በሁለተኛው አጠቃላይ ጉባኤ ስለተላለፉት ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባራዊነት አጠቃላይ ሪፖርት ተሰምቷል ።

፫ · ፲ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ/ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አማካይነት ዝርዝርና አጠቃላይ ዓመታዊ ሪፖርት ተሰምቷል ። ከየሀገረ ስብከቱም ዓመታዊ ሪፖርት ቀርቧል ። በዓመቱ የተፈጸመው የሥራ ውጤት በሚከተለው ሥዕላዊ መግለጫና አሐዛዊ ሠንጠረዥ ተገልጿል ።

## ሰበካ ጉባኤያት የተቋቋሙባቸውና ት/ቤቶች የአላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ (፲፱፻፸፯ ዓ. ም.)

| ተ. ቁ. | ሀገረስ ብከት | ሰበካ ጉባኤ የተቋቋመባቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | ቋሚ የቤተ ክ/ መንፈሳዊ ት/ ቤት የአላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | የሰንበት ት/ ቤት የአላቸው አብያተ ክርቲያናት ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 114 | 29 | 31 |
| 2 | ሲዳሞ | 224 | 25 | 53 |
| 3 | ሸዋ | 2773 | 320 | 72 |
| 4 | ባሌ | 91 | 8 | 15 |
| 5 | ትግራይ | 417 | 305 | 194 |
| 6 | አርሲ | 271 | 21 | 8 |
| 7 | አሰብ | 1 | 1 | 1 |
| 8 | አዲስአበባ | 41 | 34 | 38 |
| 9 | ኢሉባቦር | 170 | 2 | 29 |
| 10 | ኤርትራ | 80 | 46 | 21 |
| 11 | ከፋ | 279 | 92 | 68 |
| 12 | ወለጋ | 538 | 26 | 17 |
| 13 | ወሎ | 1555 | 528 | 148 |
| 14 | ጋሞጎፋ | 115 | 10 | 36 |
| 15 | ጎንደር | 2913 | 2013 | 1197 |
| 16 | ጐጃም | 2779 | 2076 | 1707 |
| | ድምር | 12361 | 5536 | 3635 |



## በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ የካህናትና የምእመናን ብዛት የ፲፱፻፸፯ ዓ/ም

| ተራ ቁ/ | የሀገረ ስብከቱ ስም | ቀሳውስት ከነ አስተዳዳሪው | ዲያቆናት | ቋሚ የቤ/ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት መምህራን | መዘምራን | ልዩ ልዩ ሠራተኞች | የአገልጋዮች ጠቅላላ ድምር | በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ ምእመናን ብዛት በጠቅ ቤተሰቦቻቸውን ሳይጨምር | በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ የካህናትና የምእመናን ቤተሰብ | የካህናትና የምእመናን ብዛት ከነ ቤተሰቦቻቸው ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረርጌ | 469 | 423 | 32 | 260 | 279 | 1467 | 41817 | 116257 | 159537 |
| 2 | ሲዳሞ | 486 | 577 | 27 | 182 | 493 | 1765 | 68830 | 226349 | 296944 |
| 3 | ሸዋ | 13838 | 13301 | 330 | 10560 | 7328 | 45357 | 643462 | 2127690 | 2816509 |
| 4 | ባሌ | 278 | 314 | 11 | 134 | 192 | 929 | 20998 | 93225 | 115152 |
| 5 | ትግራይ | 7216 | 5170 | 411 | 1115 | 823 | 14735 | 86147 | 267107 | 367989 |
| 6 | አርሲ | 1478 | 1241 | 23 | 747 | 547 | 4036 | 95078 | 354938 | 454052 |
| 7 | አሰብ | 10 | 9 | 1 | 4 | 3 | 27 | 3155 | 12620 | 15802 |
| 8 | አዲስ አበባ | 478 | 373 | 113 | 434 | 565 | 1963 | 141811 | 554444 | 698218 |
| 9 | ኢሉባቦር | 448 | 316 | 4 | 273 | 173 | 1215 | 50309 | 148530 | 200054 |
| 10 | ኤርትራ | 2768 | 1824 | 105 | 509 | 311 | 5518 | 66698 | 467473 | 539689 |
| 11 | ከፋ | 666 | 635 | 17 | 323 | 589 | 2230 | 62493 | 229253 | 293976 |
| 12 | ወለጋ | 1199 | 1536 | 11 | 324 | 623 | 3693 | 113379 | 322809 | 439881 |
| 13 | ወሎ | 21300 | 8558 | 627 | 7314 | 4253 | 42052 | 215430 | 662389 | 919871 |
| 14 | ጋሞጎፋ | 243 | 289 | 12 | 129 | 136 | 809 | 37751 | 101270 | 139830 |
| 15 | ጎንደር | 25739 | 19918 | 2711 | 12716 | 7304 | 68388 | 489318 | 1069534 | 1627240 |
| 16 | ጐጃም | 23322 | 13244 | 2941 | 16408 | 5759 | 61674 | 424986 | 1584357 | 2071017 |
| | ጠ/ ድምር | 99938 | 67728 | 7377 | 51431 | 29378 | 255854 | 2561662 | 8338245 | 11155761 |



www.ethiopianorthodox.org

## በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብ ገቢ መግለጫ ሠንጠረዥ ።

(፲፱፻፹፯ ዓ. ም.)

| ተ ቁ | ሀገረስብከት | ከሰ/መ/ት የአባልነት ክፍያ | | ከስእለት ፤ ከሙዳየ ምጽዋትና ከልዩ ልዩ ገቢ | | የገቢ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 152309 | 85 | 199817 | 28 | 352127 | 13 |
| 2 | ሲዳሞ | 151471 | 30 | 185265 | 44 | 336736 | 74 |
| 3 | ሸዋ | 2714053 | 40 | 320503 | 46 | 3034556 | 86 |
| 4 | ባሌ | 109322 | 06 | 13046 | 55 | 122368 | 61 |
| 5 | ትግራይ | 255030 | 30 | 200043 | 82 | 455074 | 12 |
| 6 | አርሲ | 272414 | 99 | 34861 | 82 | 307276 | 81 |
| 7 | አሰብ | 15799 | 75 | 30166 | 15 | 45965 | 90 |
| 8 | አዲስ አበባ | 597241 | 38 | 2873573 | 01 | 3470814 | 39 |
| 9 | ኢሉባቦር | 43230 | 85 | 50909 | 38 | 94140 | 23 |
| 10 | ኤርትራ | 121274 | 13 | 635071 | 77 | 756345 | 90 |
| 11 | ከፋ | 196109 | 37 | 117537 | 72 | 313647 | 09 |
| 12 | ወለጋ | 107419 | 85 | 93212 | 05 | 200631 | 90 |
| 13 | ወሎ | 313427 | 01 | 168354 | 17 | 481781 | 18 |
| 14 | ጋሞጎፋ | 30618 | 84 | 50140 | 77 | 80759 | 61 |
| 15 | ጎንደር | 431225 | 37 | 310501 | 15 | 741726 | 52 |
| 16 | ጐጃም | 2292793 | 35 | 228774 | 65 | 2521568 | 00 |
| | ጠቅላላ ድምር | 7803741 | 80 | 5511779 | 19 | 13315520 | 99 |



## በቅጽ « ሀ » የተመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብ ወጪ መግለጫ ሠንጠረዥ

(፲፱፻፹፯ ዓ/ም)

| ተቁ | ሀገረ ስብከት | አጥቢያው ለወረዳው የሚከፍለው 10% | | ለደመወዝ | | ለሥራ ማስኬጃ | | ልዩ ልዩ ወጪ | | የወጪ ጠቅላላ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 35212 | 71 | 254939 | 65 | 20742 | 20 | 23681 | 75 | 334576 | 31 |
| 2 | ሲዳሞ | 33673 | 65 | 212066 | 35 | 26212 | 80 | 30241 | 49 | 302194 | 29 |
| 3 | ሸዋ | 303545 | 81 | 1855625 | 10 | 388224 | 60 | 314165 | 55 | 2861561 | 06 |
| 4 | ባሌ | 12237 | 04 | 77295 | 00 | 7399 | 64 | 8882 | 35 | 105814 | 03 |
| 5 | ትግራይ | 45507 | 38 | 263845 | 57 | 62512 | 81 | 31389 | 74 | 403255 | 50 |
| 6 | አርሲ | 30727 | 64 | 198508 | 94 | 31597 | 32 | 26391 | 53 | 287225 | 43 |
| 7 | አሰብ | 4596 | 59 | 14651 | 00 | 7165 | 86 | 5646 | 95 | 32060 | 40 |
| 8 | አዲስ አበባ | 345733 | 60 | 2642114 | 68 | 252262 | 51 | 404120 | 38 | 3644231 | 17 |
| 9 | ኢሉባቦር | 9413 | 94 | 44832 | 70 | 10723 | 81 | 7471 | 86 | 72442 | 31 |
| 10 | ኤርትራ | 75634 | 59 | 438272 | 75 | 37539 | 59 | 139130 | 21 | 690477 | 14 |
| 11 | ከፋ | 31364 | 70 | 178653 | 08 | 27592 | 47 | 26065 | 60 | 263675 | 85 |
| 12 | ወለጋ | 20063 | 19 | 125189 | 97 | 18034 | 17 | 17465 | 43 | 180752 | 76 |
| 13 | ወሎ | 48182 | 42 | 224268 | 23 | 69737 | 70 | 82067 | 80 | 424256 | 22 |
| 14 | ጋሞጎፋ | 8075 | 92 | 36056 | 61 | 6359 | 71 | 14756 | 15 | 65248 | 39 |
| 15 | ጎንደር | 74172 | 62 | 241936 | 27 | 116602 | 67 | 166319 | 91 | 599031 | 47 |
| 16 | ጐጃም | 248532 | 74 | 1280840 | 51 | 352477 | 13 | 249974 | 15 | 2131824 | 53 |
| | ጠቅላላ ድምር | 1326674 | 54 | 8089096 | 41 | 1435184 | 99 | 1547257 | 85 | 12398626 | 86 |



www.ethiopianorthodox.org

## በቅጽ «ሀ» የተመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ የገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲሁም ከወጪ ቀሪ መግለጫ ሠንጠረዥ

(፲፱፻፹፮ ዓ/ም)

| ተ ቁ | ሀገረ ስብከት | የገቢ ጠቅላላ ድምር | | የወጪ ጠቅላላ ድምር | | ከወጪ ቀሪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 352127 | 13 | 334576 | 31 | 17550 | 82 |
| 2 | ሲዳሞ | 336736 | 74 | 302194 | 29 | 34542 | 45 |
| 3 | ሸዋ | 3034556 | 86 | 2861561 | 06 | 172995 | 80 |
| 4 | ባሌ | 122368 | 61 | 105814 | 03 | 16554 | 58 |
| 5 | ትግራይ | 455074 | 12 | 403255 | 50 | 51818 | 62 |
| 6 | አርሲ | 307276 | 81 | 287225 | 43 | 20051 | 38 |
| 7 | አሰብ | 45965 | 90 | 32060 | 40 | 13905 | 50 |
| 8 | አዲስ አበባ | 3470814 | 39 | 3644231 | 17 | | |
| 9 | ኢሉባቦር | 94140 | 23 | 72442 | 31 | 21697 | 92 |
| 10 | ኤርትራ | 756345 | 90 | 690477 | 14 | 65868 | 76 |
| 11 | ከፋ | 313647 | 09 | 263675 | 85 | 49971 | 24 |
| 12 | ወለጋ | 200631 | 90 | 180752 | 76 | 19879 | 14 |
| 13 | ወሎ | 481781 | 18 | 424256 | 22 | 57524 | 96 |
| 14 | ጋሞ ጎፋ | 80759 | 61 | 65248 | 39 | 15511 | 22 |
| 15 | ጎንደር | 741726 | 52 | 599031 | 47 | 142695 | 05 |
| 16 | ጉጃም | 2521568 | 00 | 2131824 | 53 | 389743 | 47 |
| | ድ ም ር | 13315520 | 99 | 12398626 | 86 | 1090310 | 91 |

ማሳሰቢያ ፡-

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከ፲፱፻፹፮ ዓ. ም. ገቢው ላይ በ፲፱፻፹፮ ዓ. ም. ተጨማሪ ወጪ በማድረጉ የ፲፱፻፹፮ ዓ. ም. ወጪ ከገቢው በላይ ብልጫ ሊያሳይ ችሏል ።

[illegible] ሦስተኛው መደበኛ ጉባኤ የቀረበለትን ሪፖርት ካዳመጠና ከተወያየበት በኋላ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል ።

[illegible] ሦስተኛው መደበኛ አጠቃላይ ጉባኤ ያሳለፈው ውሣኔና ዓመታዊ የሥራ መመሪያ ፤

ሀ/ በሀገሪቱ በደረሰው ድርቅ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ርዳታ እንዲደረግላቸው ፤

ለ/ በየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት የስብከተ ወንጌል ተጠሪ እንዲመደብ ፤

ሐ/ ሥልጣነ ክህነትና የስብከት ችሎታ የሌላቸው ሊቃነ ካህናት ችሎታቸው በሚፈቅድው ቦታ እንዲመደቡ ፤

መ/ የመደበኛ መምህራን በጀት በልዩ ልዩ ምክንያት እንዳይታጠፍና ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ፤

ሠ/ የመምህራንን የሥራ ፍሬ ተከታትሎ የሚመዘግብና የሚያስፈጽም በየሀገረ ስብከቱ የትምህርት ክፍል ተጠሪ እንዲመደብ ፤

ረ/ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጀምሮ በየደረጃው የተቋቋሙት ሰበካ ጉባኤያት የገንዘብና የንብረት ገቢና ወጪ ሂሳብ አያያዛቸው ሕጋዊነት እንዲኖረውና የቤተ ክርስቲያን ሀብት በከንቱ እንዳይባክን በማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በተዘጋጁት የገቢና ወጪ ሞዴሎች እንዲሰበሰብ ፤

ሰ/ የቤተ ክርስቲያንን ማዕከላዊ አስተዳደር ለማጠናከር በቃለ ዓዋዲ ማሻሻያ በፊደል ተራ (ሰ) በተመለከተው መሠረት ከማናቸውም ገቢ 10% በየደረጃው እንዲከፈል ፤

ሸ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ በረ ፓትርያርክ ላሉት የሂሳብ ሠራተኞች በባለሙያዎች ልዩ ልዩ ሥልጠና ተደርጎላቸው የሰበካ ጉባኤው የሥራ ይዞታ ጥራት ያለውና አስተማማኝ እንዲሆን ፤

ቀ/ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ጎትመታቸው አልቆ በስርጭት ላይ የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማሳተሚያ ድርጅቱ እየተረከበ በመውሰድ በየአውራጃውና በየወረዳው ውስጥ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት እንዲያዳርስ ፤

በ/ የካህናት አቀጣጠር ፣ የትምህርት ደረጃንና የአገልግሎት ዘመንን ፣ የሥራ አፈጻጸምንና የሥነ ሥርዓት አክባሪነትን ሁኔታ ሁሉ ያሟላ ሊሆን ስለሚገባው ፣ የመማር ጥቅሙ ያለመማር ጉዳቱ እንዲ ታወቅና ማንኛውም ካህን ዕውቀቱን ለማሻሻል ጥረት እንዲያደርግ ለጉባኤ መምህራን ማለት ለትርጓሜ መጻሕፍት ፣ ለቅኔ፣ ለዐዋትወ ዜማ ፣ ለቅዳሴና ለአቋቋም መምህራን የሚደረገው የደመወዝ አመዳደብ በ፩ኛ ደረጃ እንዲያዝ ፤

ተ/ የመሪጌትነትና የስብከት ሙያን የያዙና በማሰልጠኛዎች ሰልጥነው የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ካህናት የሁለተኛ ደረጃ አመዳደብ እንዲኖራቸው ፤

ቸ/ ቅኔ የሚቀኙ ዲያቆናትና መዘምራን ሦስተኛ ደረጃ ፣

ኀ ቅኔ የማይቀኙ ዲያቆናትና መዘምራን አራተኛ ደረጃ እየያዙ እንዲቀጠሩ ።

ነ/ በቤተ ክርስቲያን ስም በሚካሄደው የሕፃናት ማሳደጊያ ለሚረዱ ሕፃናት የግብረ ገብ ትምህርት እንዲሰጣቸው ።

ኘ/ ቅርሳቅርሶችን ለመጠበቅና በጥንቃቄ ለመመዝገብ የሚያስችል በጀት እንዲመደብ ፣

አ/ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንመንፈሳዊ ጉባኤ የስብሰባ ጊዜ በየዓመቱ በጥቅምት ወር በሚደረገው የቅ/ሲኖዶስ ስብሰባ ጊዜ እንዲሆን ።፤

ከ/ የየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናት የነፍስ ልጆቻቸውን ለሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት እያቀረቡ እንዲያስመዘግቡ ፤

ኸ/ ደረጃ በደረጃ የተቋቋሙት ሰበካ ጉባኤያት ስብሰባ እያደረጉ ስለተወያዩባቸው ጉዳዮች ሪፖርት እንዲያቀርቡ ።

ወ/ ሰበካ ጉባኤያትን ለማጠናከርና ለማደራጀት በየጊዜው የሚደረገው የሥራ ስምሪት ተልእኮ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ስለሆነ ወደፊትም እንዲቀጥል በሚሉ ዓበይት ነጥቦችና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አስተላልፎአል ።

## ፬ / የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ፬ኛ መደበኛ ስብሰባ ፤

፬ . ፩ ፬ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዓመታዊ ዓቢይ ጉባኤ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ መንበርነት ፣ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የቤተ ክርህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ የፕሮግራም መሪነት ፣ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አዘጋጅነት ፣ ከየካቲት ፳፱ እስከ የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ/ም በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተካሄዷል ።

፬. ፪ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያው ኃላፊዎች ፣ የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ካህናት ፣ የካህናትና የምእመናን ተወካዮችና የሰንበት ት/ቤቶች ተጠሪዎች በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል ።

እንዲሁም በአንደኛው ፣ በሁለተኛውና በሦስተኛው አጠቃላይ ጉባኤ እንደ ተደረገው ሁሉ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተመልካችነት በጉባኤው ላይ የተገኙ ሲሆን



www.ethiopianorthodox.org

በየጉባኤው መጨረሻ ዕለት የአዲስ አበባ አድባራት አስተዳዳሪዎችና ም/ሊቃነ መና ብርት በተመልካችነት ተገኝተዋል ።

፬.፫ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያ ጅና የጉባኤው ዋና ጸሐፊ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው አጠቃላይ ሪፖርት ካቀ ረቡ በኋላ ከመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባ ላት በሦስቱም ጠቅላላ ጉባኤያት የተሰጡ ትን ውሳኔዎችናመመሪያዎች ተግባራዊነት የሚመለከት አጠቃላይ ዝርዝር ሪፖርት ቀርቧል ።

፬.፬ ከየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ካህናት የቀረበ ዓመ ታዊ ሪፖርት ተሰምቷል ።

፬.፭ ፬ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ጉባኤ በዕለቱ የቀረቡትን ሪፖርቶች ካዳመጠ በኋላ በአንደኛው ፥ በሁለተኛውና በሦተኛው ጉባኤ ተላልፈው ተግባራዊ ባልሆኑት ጉዳ ዎች ላይ በሰፊው ተወያይቶ ውሳኔና መመሪያ ሰጥቷል ።

፬.፮ <u>በአራተኛው አጠቃላይ መደበኛ ጉባኤ የተ ላለፈ ውሳኔና መመሪያ ፤</u>

ሀ/ በድርቅ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገ ኖች የሚደረገው ርዳታ እንዲቀጥል ፤

ለ/ በመልሶ ማቋቋሙ ፕሮግራም ቤተ ክርስ ቲያናችን የምታደርገው ተሳትፎ ከፍ እን ዲል ፤

ሐ/ በየሰፈራ ጣቢያው የሚገኙ ምእመናን በየ ሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት እየተጠና መን ፈሳዊ አገልግሎት የሚያገኙበት መንገድ እንዲፈለግ ፤

መ/ ከየማሰልጠኛው ተመርቀው የሚወጡትካህ ናት ችሎታቸው እየተመዘነ በየአጥቢያቸው ያሉትን ምእመናን እንዲያስተምሩ ጥረት እንዲደረግ ፤

ሠ/ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መን ፈሳዊ ጉባኤ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ የሰባክያነ ወንጌል ተሳትፎ እንዲኖር ፤

ረ/ የቤተ ክርስቲያናችን ጋዜጦችና መጽሔቶች ስርጭት ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ከፍ ተኛ አስተዋጽኦ ያለው ስለሆነ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት አቅሙ በሚፈቅደው መጠን ኮታ እየተሰጠው የስርጭቱ ተግባር እንዲ ፋጠን እንዲደረግ ፤

ሰ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በየደረ ጃው በተመሠረቱት ሰበካ ጉባኤያት በሚ ገኘው ገቢ የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አቅም በሚፈቅደው መጠን ለመምህራኑ ደመወዝ፤

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውየጉባኤው ዋና ጸሐፊና የፕሮግራሙ መሪ በአራተኛው የመንበረ ፓትርያርክ ስብሰባ መግለጫ ሲሰጡ ።



ለተማሪዎች በዓመት ልብስ በመስጠት በቂ ክብካቤ እንዲደረግላቸው ፤

ሸ/ በዚህ ዓመት በሁሉም አብያተ ክርስቲያ ናት በቃለ ዓዋዲው ደንብ በምዕራፍ ፬ በአ ንቀጽ ፲፱ የተዘረዘሩት አሥራ አንዱ ንኡ ሳን የሥራ ክፍሎች በቂ የሰው ኃይል ባለ በት ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ ክፍል ራሱን ችሎ በቂ የሰው ኃይል በሌለበት ቦታ ደግሞ ተመሳሳይ የሥራ ጠባይ ያላቸው ክፍሎች ተደራርበው ሥራው እንዲካሄድ እንዲደ ረግ ፤

ቀ/ የመቈጣጠሪያ ክፍሉ ግን ራሱን ችሎ እንዲ ቋቋም ፤

በ/ ቀደም ብለው የተቋቋሙት የንብረትና የዕቃ ግምጃ ቤት እንዲሁም የሒሣብ ክፍል ተጠ ናክረው እንዲሠራባቸው ፤

ተ/ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚ ዘምሩት መዝሙር ያሬዳዊና የቤተ ክርስቲ ያናችንን መዝሙር ጠባይ የተከተለ እንዲ ሆን ጥንቃቄ እንዲደረግ ፤

ቸ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትር ያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለዚህ ዓቢይና ታሪካዊ ጉባኤ ያስተላለፉትን ቀ ዋሚ መመሪያና የቃለ ዓዋዲውንም ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ በ፲፮ቱም አህጉረ ስብ ከት ባሉት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያ ናት የሰንበት ትምህርት ቤት እንዲቋቋ ምና የመማሪያ መጻሕፍትም በየደረጃው እንዲዘጋጁ ፤

ኀ/ በየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ተጠሪ እንዲኖር ፤

ነ/ የቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናት በመንፈሳዊ እውቀት ታንጸው ማደግ ስለሚኖርባቸው የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ በተቋቋመባቸው አህጉረ ስብከት በፕሮግራም ተይዞ የግብረ ገብ ትምህርት እንዲሰጥ ፤

ኘ/ ከቅዱስ ፓትርያርኩ በተሰጠው መመሪያ መሠረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተዘጋጅተው የታተሙትን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምእ መናን እንዲገለገሉባቸው ማድረግ መንፈ ሳዊ ግዴታ መሆኑ ታውቆ የታተሙት መጻ ሕፍት ለየሀገረ ስብከቱ ተከፋፍለው በውስ ጣቸው ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲዳረሱ እንዲደረግ ፤

አ/ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በወረዳ በአውራጃና በሀገረ ስብከት ደረጃ ያሉት ሰበካ ጉባኤያት ሁሉ ታትመው ለሚወ ጡት መጻሕፍት ፥ መጽሔቶችና ጋዜጦች ማንበቢያና መሸጫ ቤተመጻሕፍት እንዲ ያቋቁሙ ፤

ከ/ የሠራተኞች አመዳደብና የደመወዝ ጭማ ሪው ድልድል ዘላቂነት እንዲኖረውና በየም ክንያቱ አወዛጋቢ ሁኔታዎችን ማስከተሉ እንዲቋረጥ ከሕጉ ጋር እየተገናዘበ በመ ላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት የቅጥርና የደመወዝ ጭማሪ መነሻና መድረሻ ጣራ ያለው መመ ሪያ እንዲወጣ ፤

ኸ/ የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳትና ቅር ሳቅርሶችን በየመልክ በየመልካቸው የሚመ ዘግቡና በቀዋሚነት የሚሠሩ ቋም ጸሐፊ ዎች በየሀገረ ስብከቱ እንዲቀጠሩ ፤

ወ/ የልማት ተግባሮች ለቤተ ክርስቲያናችን የገቢ ምንጭ ማዳበሪያ ከመሆናቸውም በላይ ራስን ለመቻል የሚያግዙ ስለሆኑ የተጀመ ረው የልማት ተግባር እንዲቀጥልና አጥ ጋቢ ውጤትም እንዲኖረው በየደረጃው የል ማት ኮሚቴ እንዲቋቋም ፤

ዐ/ የሰበካ ጉባኤያትን ጥንካሬ ለመገምገምና ለመለካት ከስምሪት አንድ እስከ ስምሪት አምስት በተካሄደው ሐዋርያዊ ተልእኮ ፍሬ ያማ ውጤት መገኘቱ የተረጋገጠ ስለሆነ አሁንም የተልእኮው አመርቂነት ታምኖ በት የስምሪት ስድስትና ሰባት ተልእኮ እን ዲቀጥል በማለት ውሳኔዎችንና መመሪያ ዎችን አስተላልፎአል ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁኖ በቤተ ክርስቲያ ናችን የተደረገው የአስተዳደር ተሐድሶ ካስገኛቸው ውጤቶች አንዱ በቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር ማዕከላዊ አሠራርን በማስፈንና ከዚያም የሰውንና የገንዘብ ኃይልን በማስተባበር ለቤተ ክርስቲያና ችን ዕድገትና ጥንካሬ አስተማማኝ የሆነ መሠረት ለመጣል ያስቻለው የሰበካ ጉባኤ መዋቅር ነው ። የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ አሻሽሎ ባወ ጣው ቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት ከአጥቢያ ቤተ ክር ስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ በየደረጃው የተቋቋመው ሰበካ ጉባኤ ሁሉም ጾታ ምእመናን ማ ለት ካህናትና ምእመናን ፥ አበውና ውሉድ ፥ ሴቶ



www.ethiopianorthodox.org

ችና ወንዶች በአንድ ላይ ተሰብስበው ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት መሟላት በአንድነት የሚመካከሩበትና የሚወስኑበት የአስተዳደር መዋቅር በመሆኑ ራስን በመቻል አንፃር በአሁኑ ጊዜ ከዚህ ደረጃ መድረስ የተቻለው በሁሉም ጾታ ምእመናን ተወካዮች ተሳታፊነትና በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርካችን ሊቀ መንበርነት በተካሄዱት በእነዚህ አራት ጉባኤያት የተሰጡትን መመሪያዎች በመከተል በተፈጸመ የሥራ ክንውን መሆኑ ግልጽ ነው ።

ስለዚህ እስከ አሁን በተከታታይ በተደረጉት አራት ጉባኤያት በተቀየሰው መርሐ ግብር አፈጻጸም ይህን ያህል ውጤት ከተገኘ ወደፊት በሚደረጉት ጉባኤያት በሚሰጡት መመሪያዎች መሠረት በሚፈጸመው የሥራ ክንውን ደግሞ እስከ አሁን ያልተፈጸሙትን ድምር ሥራዎች በማጠናቀቅ ከታሰበው የዕድገትና ጥንካሬ ደረጃ ማለት ቤተ ክርስቲያናችን አሁን ከምትገኝበት የተረጂነት ደረጃ አልፋ ራስዋን ለመቻል ለሌላው ለመትረፍ ወደ ምትችልበት ደረጃ ደርሳ ለማየት የሚቻልበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን የሁሉም እምነት ነው ።

<u>በሰንጠረዥ የተገለጸው የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም የገንዘብና የሰው ኃይል በአማካይ ድርሻ ሲተመን የሚያሳየው ሂሣብ ፤</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩/ | ካለፈው ዓመት ከወጪ ቀሪ ሆኖ ለ፲፱፻፹፰ ዓ/ም የዞረ | ብር | 2477970 . 58 |
| ፪/ | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም የዘመኑ ገቢ | ብር | 16126324 . 19 |
| | ጠቅላላ የገቢ ድምር | ብር | 18604294 . 77 |
| ፫/ | ጠቅላላ ገቢው በሙሉው ዐበይት ርእሶች ሲመደብ ፤ | | |
| ሀ/ | ከዘመኑ ገቢ ላይ ለወረዳ 10% | ብር | 1588640 . 82 |
| ለ/ | ለደመወዝ | ብር | 9513761 . 28 |
| ሐ/ | ለሥራ ማስኬጃ | ብር | 1955791 . 47 |
| መ/ | ለልዩ ልዩ ወጭ | ብር | 2134888 . 54 |
| ሠ/ | ከወጭ ቀሪ | ብር | 3411212 . 66 |
| | ድምር | ብር | 18604294 . 77 |

፬/ ይህም አጠቃላይ ሂሣብ በቅጽ (ሀ) ተመዝግበው 10% ለከፈሉት አብያተ ክርስቲያናት ሲተነተን ፤

ሀ/ በሰንጠረዥ ላይ ለደመወዝ የተመለከተው - - - ብር 9513761-28ለ276709 አገልጋዮች ሲከፈል የአንድ ሰው ድርሻ ፤

ለወር ---- ብር 2.87 ለዓመት ---- ብር 34.38

ለ/ ለሥራ ማስኬጃ የተመለከተው ብር 1955791.47 በቅጽ(ሀ)ለተመዘገቡትና 10%ለከፈሉት ለ13905 አብያተ ክርስቲያናት ሲከፈል የአንድ ቤተክርስቲያን ድርሻ ፤

ለወር . .... ብር 11.72 ለዓመት ---- ብር 140.65

ሐ/ ለልዩ ልዩ ወጭ የተመለከተው ብር 2134888.54 ለ13905 አብያተ ክርስቲያናት ሲተነተን የአንድ ቤተክርስቲያን ድርሻ ፤

ለወር ---- ብር 12.79 ለዓመት ----- ብር 153.53

መ/ በሰንጠረዥ የተገለጸው ከወጪቀሪ ብር 3411212.66 በቅጽ(ሀ)ለተመዘገቡትና 10% ለከፈሉት አብያተ ክርስቲያናት ሲከፈል 3411212÷ 13905

ለወር ----- ብር 20.44 ለዓመት ----- ብር 245.32

ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው ክፍያ ለተጠቀሱት ካህናትና አብያተ ክርስቲያናት በቂ መተዳደሪያ ይሆናል ተብሎ አይገመትም ። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያኒቱ በዚህን ያህል ካህናት የምትገለገለው አብዛኛዎቹ አሁንም በእርሻና በልዩ ልዩ የግል ሥራ ስለሚተዳደሩ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ቅጽ ሠ—፩ኛ
ቁጥር ፩

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ

# የጠቅላላው አብያተ ክርስቲያናት ፤ የካህናትና የምእመናን ብዛት ምዝገባ ማጠቃለያ ቅጽ

| | | (ሀ) ጠቅላላ የየሀገረ ስብከቱ አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | | | | | | | | | | | | | | | (ለ) ጠቅላላ የካህናትና ምእመናን ብዛት | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በሀገረ ስብከቱ ውስጥ | | | | | | | | | | | | | በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚገኙ የአብያተ ክ/አገልጋዮች ብዛት | | | | | | በሀገረ ስብከቱ አብያተ ክርስቲያናት | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ ምእመናን ብዛት | | በሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገቡ ምእመናን ብዛት | | | |
| ተራ ቁጥር | የሀገረ ስብከቱ ስም | [illegible] | [illegible] | ጠቅላላ የአብያተ ክርስቲያናት ብዛት | በቅጽ (ሀ) የተመዘገቡ አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | የገዳማት ብዛት | የአድባራት ብዛት | የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ብዛት | ቀሳውስት (ከነአለቆቻቸው) | ዲያቆናት | [illegible] | መዘምራን | [illegible] | የአገልጋዮቹ ብዛት ድምር | የአገልጋዮች ቤተ ሰብ ብዛት | በጠ.ሰ | በቤተ ሰብ | በ ጠ. ሰ | በቤተ ሰብ | የካህናትና የምእመናን ብዛት ከነቤተሰቦቻቸው ጠቅላላ ድምር | ምርመራ |
| 1 | ሐረርጌ | 11 | 35 | 119 | 119 | 113 | 6 | 27 | 92 | 33 | 86 | 4 | 27 | 88 | 424 | 436 | 30 | 243 | 320 | 1453 | 3124 | 40335 | 126748 | 22486 | 73245 | 267391 | |
| 2 | ሲዳሞ | 7 | 31 | 239 | 236 | 236 | 3 | 28 | 211 | 70 | 169 | 1 | 16 | 222 | 498 | 609 | 32 | 216 | 511 | 1866 | 5309 | 73279 | 219806 | 8284 | 24993 | 333537 | |
| 3 | ሸዋ | 11 | 100 | 2869 | 2867 | 2844 | 25 | 346 | 2523 | 165 | 2704 | 89 | 202 | 2578 | 13813 | 13570 | 523 | 10709 | 7458 | 46073 | 128413 | 595909 | 1925959 | 127018 | 356508 | 3179880 | |
| 4 | ባሌ | 5 | 15 | 93 | 93 | 93 | — | 6 | 87 | 15 | 78 | — | 7 | 86 | 294 | 327 | 9 | 171 | 312 | 1113 | 2125 | 19971 | 79572 | 3161 | 7364 | 113306 | |
| 5 | ትግራይ | 9 | 55 | 3720 | 696 | 688 | 3032 | 429 | 3291 | 233 | 3487 | 181 | 224 | 3315 | 12235 | 8972 | 582 | 1542 | 1142 | 24473 | 83818 | 135993 | 467929 | 1222 | 3883 | 717318 | |
| 6 | አርሲ | 4 | 26 | 274 | 274 | 274 | — | 27 | 247 | 9 | 265 | 1 | 16 | 257 | 1421 | 1192 | 28 | 610 | 536 | 3787 | 10797 | 98980 | 357781 | 9798 | 26159 | 507302 | |
| 7 | አሰብ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | — | 1 | — | 1 | — | — | 1 | — | 10 | 9 | 3 | 3 | 5 | 30 | 64 | 3803 | 15102 | 80 | 131 | 19210 | |
| 8 | አዲስ አበባ | 5 | 44 | 49 | 44 | 43 | 6 | 34 | 15 | 44 | 5 | 11 | 37 | 1 | 528 | 378 | 110 | 446 | 579 | 2041 | 4601 | 132269 | 617809 | 176890 | 579782 | 1513392 | |
| 9 | ኢሉባቦር | 6 | 35 | 178 | 177 | 177 | 1 | 7 | 171 | 37 | 141 | — | 8 | 170 | 574 | 425 | 9 | 474 | 240 | 1722 | 4776 | 50833 | 141571 | 44051 | 91784 | 334737 | |
| 10 | ኤርትራ | 9 | 18 | 1050 | 707 | 114 | 936 | 107 | 943 | 26 | 1024 | 20 | 71 | 959 | 6802 | 4395 | 396 | 1231 | 1366 | 14190 | 56190 | 28972 | 138534 | 197091 | 856612 | 1291589 | |
| 11 | ከፋ | 6 | 34 | 287 | 282 | 282 | 5 | 26 | 261 | 31 | 256 | 1 | 29 | 257 | 751 | 661 | 27 | 269 | 646 | 2354 | 6049 | 63343 | 227413 | 46059 | 115072 | 460290 | |
| 12 | ወለጋ | 7 | 49 | 715 | 689 | 686 | 29 | 14 | 701 | 61 | 654 | 1 | 17 | 697 | 1529 | 1846 | 16 | 497 | 835 | 4723 | 12301 | 156891 | 495722 | 49356 | 155316 | 874309 | |
| 13 | ወሎ | 13 | 30 | 2106 | 1784 | 1776 | 330 | 394 | 1712 | 158 | 1948 | 69 | 310 | 1727 | 11729 | 8994 | 613 | 6544 | 3747 | 31627 | 86267 | 199745 | 631815 | 18314 | 54180 | 1021948 | |
| 14 | ጋሞ ጎፋ | 5 | 22 | 118 | 118 | 118 | — | 13 | 105 | 36 | 82 | 2 | 16 | 100 | 260 | 338 | 14 | 172 | 190 | 974 | 2892 | 39025 | 113996 | 18560 | 45415 | 220862 | |
| 15 | ጎንደር | 8 | 32 | 3019 | 2995 | 2941 | 78 | 2328 | 691 | 1478 | 1541 | 185 | 665 | 2169 | 28438 | 23110 | 3111 | 14709 | 8093 | 77461 | 163844 | 474296 | 1405530 | 39607 | 104842 | 2265580 | |
| 16 | ጐጃም | 8 | 36 | 2823 | 2823 | 2779 | 44 | 2240 | 583 | 1812 | 1011 | 320 | 123 | 2380 | 23653 | 13791 | 3020 | 16557 | 5801 | 62822 | 154622 | 445520 | 1636192 | 47881 | 128920 | 2475957 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 115 | 566 | 17660 | 13905 | 13165 | 4495 | 6027 | 11633 | 4209 | 13451 | 885 | 1804 | 14971 | 102.959 | 79053 | 8523 | 54393 | 31781 | 276709 | 725192 | 2559164 | 8601479 | 809858 | 2624206 | 15596608 | |

የተዘጋጀበት ______ ቀን 19[illegible] ዓ/ም

ስለ ትክክለኛነቱ የጠቅላይ ቤተ ክህነት

የአስተዳደር ... ኃላፊ ስምና ፊርማ ______

የሰበካ ጉባኤ ... ኃላፊ ስምና ፊርማ ______

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ______

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ______

www.ethiopianorthodox.org

ቅጽ ሠ—፩ኛ
ቁጥር ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ
?ጠቅላላው አብያተ ክርስቲያናት የገንዘብ ገቢና ወጪ ምዝገባ ማጠቃለያ ቅጽ

(ሀ) ጠቅላላ የምእመናን አስተዋፅኦና ... ልዩ ... ገቢ

| ተራ ቁጥር | የሀገረ ስብከቱ ስም | ከሀገረ ስብከቱ ምእመናን የተገኘ የሰበካ ጉባኤ የአባልነት ክፍያ የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ገቢ | | ከስእለት፣ ከሙዳየ ምጽዋት ከልዩ ልዩ የተገኘ ገቢ የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም | | የ... ዓ/ም የ... ገቢ ድምር | | ... | | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም የገቢ ጠቅላላ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 163216 | 70 | 260875 | 38 | 424092 | 68 | 278511 | 07 | 702603 | 15 |
| 2 | ሲዳሞ | 165716 | 65 | 189645 | 24 | 355361 | 89 | 37756 | 80 | 393118 | 69 |
| 3 | ሸዋ | 2769802 | 55 | 386958 | 93 | 3156761 | 48 | 130667 | 71 | 3287429 | 19 |
| 4 | ባሌ | 112909 | 53 | 13104 | 80 | 126014 | 33 | 17596 | 66 | 143610 | 99 |
| 5 | ትግራይ | 507936 | 24 | 274707 | 28 | 782643 | 52 | 64562 | 80 | 847206 | 32 |
| 6 | አርሲ | 203404 | 50 | 33530 | 33 | 236934 | 83 | 37135 | 26 | 274070 | 09 |
| 7 | አሰብ | 26120 | 50 | 54517 | 25 | 80637 | 75 | 13905 | 50 | 94543 | 25 |
| 8 | አዲስ አበባ | 531864 | 29 | 3081133 | 28 | 3612997 | 57 | 1055142 | 43 | 4668140 | 00 |
| 9 | ኢሉባቦር | 51377 | 44 | 70975 | 17 | 122352 | 61 | 40806 | 82 | 163159 | 43 |
| 10 | ኤርትራ | 174115 | 40 | 788255 | 57 | 962370 | 97 | 217058 | 17 | 1179429 | 14 |
| 11 | ከፋ | 186651 | 98 | 138800 | 09 | 325452 | 07 | 59947 | 54 | 385399 | 51 |
| 12 | ወለጋ | 194453 | 10 | 159897 | 90 | 354351 | 60 | 39167 | 40 | 393518 | 40 |
| 13 | ወሎ | 660866 | 27 | 228866 | 52 | 889732 | 79 | 37586 | 77 | 927319 | 56 |
| 14 | ጋሞ ጎፋ | 42631 | 25 | 52662 | 67 | 95293 | 92 | 33702 | 49 | 128996 | 41 |
| 15 | ጎንደር | 1293996 | 05 | 627348 | 56 | 1921344 | 61 | 132573 | 56 | 2053918 | 17 |
| 16 | ጐጃም | 2393560 | 90 | 286421 | 87 | 2679982 | 77 | 285849 | 60 | 2965832 | 37 |
| | ጠቅላላ ድምር | 9478623 | 35 | 6647700 | 84 | 16126324 | 19 | 2477370 | 58 | 18604294 | 77 |

(ለ) የየሀገረ ስብከቱ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ ወጪ

| ተራ ቁጥር | የሀገረ ስብከቱ ስም | ከ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ... 10% (አሥር ከመቶ) | | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም የካህናት ደመወዝ | | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም የሥራ ማስኬጃ | | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ልዩ ልዩ ወጪ | | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ወጪ ጠቅላላ ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ |
| 1 | ሐረርጌ | 42409 | 32 | 300808 | 33 | 21602 | 01 | 52999 | 23 | 417518 | 94 |
| 2 | ሲዳሞ | 32131 | 11 | 224019 | 99 | 31828 | 09 | 23523 | 73 | 311502 | 92 |
| 3 | ሸዋ | 315677 | 09 | 1871459 | 84 | 439050 | 45 | 327384 | 53 | 2953571 | 91 |
| 4 | ባሌ | 12601 | 27 | 88873 | 59 | 11801 | 26 | 10827 | 10 | 124103 | 22 |
| 5 | ትግራይ | 78264 | 27 | 523723 | 05 | 111123 | 61 | 57552 | 04 | 770663 | 07 |
| 6 | አርሲ | 23693 | 36 | 168993 | 10 | 25800 | 53 | 18560 | 09 | 237067 | 08 |
| 7 | አሰብ | 8063 | 77 | 17520 | 00 | 4898 | 20 | 13083 | 00 | 43564 | 97 |
| 8 | አዲስ አበባ | 340695 | 65 | 2892401 | 44 | 216172 | 48 | 287559 | 63 | 3736909 | 20 |
| 9 | ኢሉባቦር | 12235 | 23 | 57108 | 45 | 7140 | 78 | 27313 | 64 | 103798 | 10 |
| 10 | ኤርትራ | 96237 | 04 | 522688 | 49 | 68040 | 94 | 305434 | 24 | 992400 | 71 |
| 11 | ከፋ | 32545 | 11 | 192313 | 36 | 51305 | 09 | 35348 | 20 | 311511 | 76 |
| 12 | ወለጋ | 35451 | 92 | 179302 | 09 | 41707 | 18 | 34409 | 05 | 290870 | 15 |
| 13 | ወሎ | 88973 | 29 | 385862 | 80 | 140817 | 22 | 189452 | 47 | 805105 | 78 |
| 14 | ጋሞ ጎፋ | 9529 | 58 | 40868 | 49 | 6427 | 39 | 16265 | 71 | 73091 | 17 |
| 15 | ጎንደር | 192134 | 44 | 579005 | 25 | 377751 | 01 | 461927 | 68 | 1610818 | 38 |
| 16 | ጐጃም | 267998 | 27 | 1468733 | 10 | 400325 | 23 | 273228 | 15 | 2410284 | 75 |
| | ጠቅላላ ድምር | 1588640 | 82 | 9513761 | 28 | 1955791 | 47 | 2134888 | 54 | 15193082 | 11 |

| ተራ ቁጥር | የሀገረ ስብከቱ ስም | የ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ከወጪ ቀሪ | | ከ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ከወረዳ ... ላይ የአጥቢያ ድርሻ 50% (አምሳ ከመቶ) | | ከ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ከአውራጃው ድርሻ ላይ የሀገረ ስብከቱ ድርሻ 40% (አርባ ከመቶ) | | ከ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ከሀገረ ስብከቱ ድርሻ ላይ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ... ድርሻ 25% (ሃያ አምስት ከመቶ) | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | |
| 1 | ሐረርጌ | 284784 | 21 | -21204 | 68 | 8481 | 85 | 2120 | 46 | |
| 2 | ሲዳሞ | 81615 | 77 | 19470 | 56 | 8128 | 71 | 2032 | 18 | |
| 3 | ሸዋ | 333557 | 28 | 157838 | 65 | 63135 | 43 | 15783 | 85 | |
| 4 | ባሌ | 19507 | 77 | 6300 | 64 | 2520 | 28 | 630 | 07 | |
| 5 | ትግራይ | 72543 | 25 | 39132 | 20 | 15652 | 88 | 3913 | 22 | |
| 6 | አርሲ | 37003 | 01 | 13254 | 45 | 5301 | 76 | 1325 | 44 | |
| 7 | አሰብ | 50978 | 28 | 4031 | 88 | 1612 | 75 | 403 | 18 | |
| 8 | አዲስ አበባ | 967715 | 51 | | | 340695 | 65 | 170347 | 82 | |
| 9 | ኢሉባቦር | 59361 | 33 | 6117 | 59 | 2447 | 01 | 1223 | 50 | |
| 10 | ኤርትራ | 187028 | 43 | 48193 | 51 | 19277 | 03 | 4819 | 25 | |
| 11 | ከፋ | 73887 | 85 | 16272 | 58 | 6509 | 03 | 1627 | 25 | |
| 12 | ወለጋ | 102648 | 25 | 16150 | 24 | 9611 | 63 | 2402 | 90 | |
| 13 | ወሎ | 122213 | 78 | 45019 | 58 | 18007 | 82 | 4501 | 95 | |
| 14 | ጋሞ ጎፋ | 55905 | 24 | 4764 | 78 | 1905 | 89 | 476 | 47 | |
| 15 | ጎንደር | 443099 | 79 | 96067 | 20 | 31539 | 94 | 7884 | 98 | |
| 16 | ጐጃም | 555547 | 62 | 133999 | 13 | 53599 | 63 | 13399 | 90 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 3411212 | 66 | 627819 | 67 | 588427 | 29 | 232892 | 42 | |

ሒሳብ ትክክል ስለመሆኑ የጠቅላይ ቤተ ክህነት

...የተሞላበት ________ ፲፱፻፹፰ ዓ/ም

የበጀትና ሒሳብ ተና ክፍል ኃላፊ ስምና ፊርማ ________

የቁጥጥር አገልግሎት ኃላፊ ስምና ፊርማ ________

የአስተዳደር፣ የገንዘብና ንብረት መምሪያ ኃላፊ ስምና ፊርማ ________

(የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ ቤት ማኅተም) ________

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ________

www.ethiopianorthodox.org

**በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ የተቋቋሙት ሰበካ ጉባኤያት ደረጃ በደረጃ የሚከፍሉትንና ለራሳቸው የሚያስቀሩትን**

**የሒሳብ ድርሻ የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

የ፲፱፻፸፰ ዓ.ም.

| ተራ ቁ/ | የሀገረ ስብ ከቱ ስም | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሒሳብ — የአጥቢያ ቤ/ክ/ጠ/ ገቢ 100% | | ከአጥቢያ ለወረዳው የተከፈለ 10 % | | የአጥቢያው ቤተ ክ/ ድርሻ 90% | | የወረዳ ሒሳብ — ከገቢው 10% ላይ ወረዳው ለአውራጃው የከፈለው 5% | | የወረዳው ድርሻ 5 % | | የአውራጃ ሒሳብ — ከገቢው 5% ላይ አውራጃው ለሀ/ስብከት የከፈለው 2% | | የአውራጃው ድርሻ 3 % | | የሀገረ ስብከት ሒሳብ — ከገቢው 2 % ላይ ሀ/ስብከቱ ለመንበረ ፓትርያርክ የከፈለው 0. 5 % | | የሀገረ ስብከት ድርሻ 1. 5 % | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | ብር | ሳ | |
| 1 | ሐረርጌ | 424092 | 08 | 42409 | 32 | 381682 | 80 | 21204 | 60 | 21204 | 60 | 6361 | 39 | 12722 | 76 | 2120 | 46 | 6361 | 39 | |
| 2 | ሲዳሞ | 355361 | 89 | 32131 | 11 | 319825 | 80 | 17768 | 10 | 17768 | 10 | 6095 | 53 | 10660 | 86 | 2032 | 18 | 6095 | 53 | |
| 3 | ሸዋ | 3156761 | 48 | 315677 | 09 | 2841084 | 90 | 157838 | 05 | 157838 | 05 | 47351 | 58 | 94702 | 83 | 15783 | 81 | 47351 | 58 | |
| 4 | ባሌ | 126014 | 33 | 12601 | 27 | 113412 | 60 | 6300 | 70 | 6300 | 70 | 1890 | 21 | 3780 | 42 | 630 | 07 | 1890 | 21 | |
| 5 | ትግራይ | 782643 | 52 | 78264 | 37 | 704379 | 60 | 39132 | 20 | 39132 | 20 | 11739 | 66 | 23479 | 32 | 3913 | 22 | 11739 | 66 | |
| 6 | አርሲ | 326924 | 83 | 23693 | 36 | 213241 | 50 | 11846 | 75 | 11846 | 75 | 3976 | 32 | 7108 | 05 | 1325 | 44 | 3976 | 32 | |
| 7 | አሰብ | 80637 | 75 | 8063 | 77 | 72574 | 20 | 4031 | 90 | 4031 | 90 | 1209 | 57 | 2419 | 14 | 403 | 18 | 1209 | 57 | |
| 8 | አዲስ አበባ | 3612997 | 57 | 340695 | 65 | 3251698 | 20 | — | | —— | | 170347 | 83 | —— | | 170347 | 83 | 170347 | 83 | |
| 9 | ኢሉባቦር | 122352 | 61 | 12235 | 23 | 110117 | 70 | 6117 | 65 | 6117 | 65 | 1223 | 51 | 3670 | 59 | 1223 | 51 | 1223 | 51 | |
| 10 | ኤርትራ | 962370 | 97 | 96237 | 04 | 866133 | 90 | 48118 | 55 | 48118 | 55 | 14457 | 58 | 28871 | 13 | 4819 | 25 | 14457 | 58 | |
| 11 | ከፋ | 325452 | 07 | 32545 | 11 | 292906 | 80 | 16272 | 60 | 16272 | 60 | 4881 | 78 | 9763 | 56 | 1627 | 26 | 4881 | 78 | |
| 12 | ወለጋ | 354351 | 00 | 35451 | 92 | 318915 | 90 | 17717 | 55 | 17717 | 55 | 7208 | 73 | 10630 | 53 | 2402 | 90 | 7208 | 73 | |
| 13 | ወሎ | 889732 | 79 | 88973 | 29 | 800759 | 70 | 44486 | 65 | 44486 | 65 | 13505 | 87 | 26691 | 99 | 4501 | 95 | 13505 | 87 | |
| 14 | ጋሞጎፋ | 95293 | 92 | 9529 | 58 | 85764 | 60 | 4764 | 70 | 4764 | 70 | 1429 | 42 | 2858 | 82 | 476 | 47 | 1429 | 42 | |
| 15 | ጎንደር | 1921344 | 61 | 192134 | 44 | 1729210 | 50 | 96067 | 25 | 96067 | 25 | 23654 | 96 | 57640 | 35 | 7884 | 98 | 23654 | 96 | |
| 16 | ጐጃም | 2679982 | 77 | 267998 | 27 | 2411894 | 70 | 133999 | 15 | 133999 | 15 | 40199 | 73 | 80399 | 49 | 13399 | 90 | 40199 | 73 | |
| | ጠ/ድምር | 16126324 | 19 | 1588640 | 82 | 14513693 | 40 | 625666 | 40 | 625666 | 40 | 355533 | 67 | 375399 | 84 | 232892 | 41 | 355533 | 67 | |

ማሳሰቢያ ፡ ይህ የሂሣብ መግለጫ ሠንጠረዥ የታኅሣሥ ፲ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ቃለ ዓዋዲ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ማሻሻያ ደንብ በቍጥር ፲፪ በፊደል ተራ (ሰ) መሠረት የአስተዋጽኦው ክፍያ ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ደረጃ–በደረጃ በፐርሰንት ያለውን ድርሻ የሚያመለክት ሲሆን ፤ በዚሁ ቃለ ዓዋዲ በገጽ ፫ ላይ የየሀገረ ስብከቱ መንበረ– ጵጵስና ዋና ከተማ እንደ አንድ አውራጃ ይቈጠራል በሚለው መሠረት አንዳንዶቹ ሀገረ ስብከቶች ደንቡን ጠብቀው በዋና ዋና ከተሞች–የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ከጠቅላላ ገቢያቸው 10 % (አሥር ከመቶ) ወጭ አድርገው ለወረዳ ድርሻ ሳይቀንሱ በቀጥታ ለአውራጃው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገቢ ያደረጉ ስለሆነ ከአጥቢያ ጀምሮ በየደረጃው የሚታየውን የ10% ስሌት ማለት የአውራጃውን ፤ የሀገረ ስብከቱንና የመንበረ ፓትርያርኩን ድርሻ ከፐርሰንቱ ከፍ አድርጎት ይታያል ። የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትም 10% (አሥ ከመቶ) ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ተቀብሎ በቀጥታ ለሀገረ ስብከቱ ገቢ ካደረገ በኋላ በመቶ አምሳውን (50 %) ለመንበረ ፓትርያርኩ ገቢ የሚያደርግ በመሆኑ ሂሣቡን በዚሁ መሠረት ለማየት ይቻላል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፬

# የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሥራ እቅድና አፈጻጸም፤

በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፬ ላይ እንደተገለጸው በየደረጃው መቋቋም ከሚገባቸው ሰበካ ጉባኤያት አንዱ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ይህ አጠቃላይ ጉባኤ ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፸፰ዓ/ም በተመሠረተ ጊዜ የዚህ አካል የሆነው የአስተዳደር ጉባኤም (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፵፮ መሠረት ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ/ም በአጠቃላይ ጉባኤው በምርጫ ተሰየመ ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀመንበርነት የተመራው አጠቃላይ ጉባኤ በወቅቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን መርጦ ለመሰየም ባካሄደው ከፍተኛ የምርጫ ስነ ሥርዓት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በቃለ ዓዋዲው ደንብ በአንቀጽ ፵፯ ቁጥር ፩ መሠረት የኮሚቴው ሊቀ መንበር፣

ከካህናት፦ ፩ኛ/ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን ም/ሊቀ መንበር

፪ኛ/ ሊቀ ካህናት ክፍሌ ገ/መስቀል የኮሚቴው አባል

፫ኛ/ ሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ/ሕይወት የኮሚቴው አባል

ከምእመናን፦ ፬ኛ/ አቶ እስፋወሰን መካሻ የኮሚቴው አባል

፭ኛ/ አቶ ባርያኡ ገ/ኢየሱስ የኮሚቴው አባል

ከሰንበት ት/ቤት ፡ ፮ኛ/ አቶ ጌታቸው ዘሩ አባል

ሆነው እንዲሠሩ የተመረጡ ሲሆን ኮሚቴው በቃለ ዓዋዲው ደንብ በአንቀጽ ፵፯ ቁጥር ፫ መሠረት በሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ዋና ጸሐፊነት ሥራውን ጀምሯል ።

የምርጫው ስነ ሥርዓት እንዳበቃ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ለኮሚቴው አባላት ቡራኬ በሰጡበት ጊዜ «ምርጫ የሚደረገው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ፤ በከንቱ አይመረጥም ፣ ይህ ሁሉ በሚደረግበት ጊዜ እግዚአብሔር በመካከላችን ይኖራል ፤ የሚያስፈጽመው እሱ ነውና ፤ ለቤተ ክርስቲያን ጠንክራችሁ እንድትሠሩ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ አድሮ እናንተን የመረጣችሁ ስለሆነ ወገባችሁ የታጠቀ ፣ መብራታችሁ የበራ ይሁን» በማለት ለኮሚቴው መመሪያ ሰጥተዋል ።

የሰዎችም የእግዚአብሔርም አደራ ያለበትን ይህን ከባድ ኃላፊነት እንዲረከብ የተሰየመው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፵፯ ከ ቁጥር ፩—፲፪ የተደነገገለትን የሥልጣንና የተግባር ድርሻ ለመፈጸምና ኃላፊነቱንም ለመወጣት የሚያስችሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ለማመቻቸት ሰኔ ፫ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ/ም የመጀመሪያ ስብሰባውን አደረገ ።

፩/ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንደመሆኑ መጠን ኃላፊነቱን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ አጠቃላይ ጉባኤው በመጀመሪያ መደበኛ ስብሰባው ያሳለፋቸው ውሳኔዎችና መመሪያዎች በየሥራ መስኩ በተግባር እንዲተረጐሙ ለየመምሪያዎቹና ለየአህጉረ ስብከቱ በወቅቱ እንዲዳረሱ ፣

፪/ ሰበካ ጉባኤ ከመጠናከሩ በፊት ይሠራባቸው የነበሩ የገንዘብ መሰብሰቢያ ካርኔዎች ለዘመናዊ አሠራር አመች ባለመሆናቸው በምትካቸው ለቊጥጥርና ለአሠራር ቅልጥፍና የሚያመቹና ልዩ መለያ ቊጥር ያላቸው ካርኔዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ፣



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጎፋ ዕድጥበብ የተመረተውን ልዩ ልዩ ልብስ ሲመለከቱ



የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በሥራ ላይ እንዳሉ

፫/ የአብያተ ክርስቲያናትን ብዛት ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትንና የምእመናንን ቊጥር ፡ እንዲሁም በተለያየ መንገድ ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚገባው የገንዘብ ኃይል መጠን የሚመዘገብባቸው ቅጾች ቢዘጋጁና ቢሠራባቸው ጠቃሚ መሆኑን በማመን ከሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ በቀረበው ጥናታዊ መግለጫ መሠረት ጉዳዩ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ሲፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን ፣

፬/ የስምሪት መርሐ ግብር በመቀየስ በቃለ ዓዋዲው ደንብና አጠቃላይ ጉባኤውም ባሳለፈው ውሳኔና መመሪያ መሠረት ሰበካ ጉባኤ በየደረጃው እንዲቋቋምና እንዲጠናከር ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል ፣ እያደረገም ነው ።

በወጣው ዕቅድ መሠረትም እስከ አሁን ስድስት የሥራ ስምሪቶች በሁሉም አህጉረ ስብከት በተከታታይ ተካሂደዋል ።

የስምሪት አንድና ሁለት ተልእኮ አፈጻጸም ከመጀመሩ አስቀድሞ ተቀዳሚ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ፣

፩ኛ/ ቅጽ ሀ ቊጥር ፩ የአጥቢያ መመዝገቢያ ቅጽ
፪ኛ/ ቅጽ ለ ቊጥር ፩ የወረዳ ማጠቃለያ ቅጽ
፫ኛ/ ቅጽ ሐ ቊጥር ፩ የአውራጃ ማጠቃለያ ቅጽ
፬ኛ/ቅጽ መ ቊጥር ፩ የሀገረ ስብከትማጠቃለያ ቅጽ
፭ኛ/ ቅጽ ሠ ቊጥር ፩ የመንበረ ፓትርያርክ ማጠቃለያ ቅጽ በጠቅላላ የአብያተ ክርስቲያናት ብዛት፣ የካህናትና የምእመናን ቊጥር፣ የገንዘብ ኃይል ማለት የገቢና የወጭ መጠን የሚመዘገቡባቸው አምስት ዓይነት ቅጾች ተዘጋጅተውና ታትመው ለየሀገረ ስብከቱ እንዲሰራጩ አድርጓል ።

### ፩ኛ/ የስምሪት ፩ እና ፪ ተልእኮ አፈጻጸም፡

ስምሪት አንድንና ሁለትን በተሟላ ሁኔታ ለማካሄድ ብዙ የሥራ ልምድና የዳበረ ችሎታ ያላቸው ከቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ ባለሙያዎችን በማሰባሰብ በልዩ ሰሚናር ስለስምሪቱ ተልእኮ አፈጻጸም ጠቃሚ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጎአል ።

በዚህ መልክ የሰለጠኑትን የመንበረ ፓትርያርክ ልኡካን ወደየሀገረ ስብከቱ በማሰማራትና ስምሪቱም እስከ አውራጃዎች ድረስ እንዲዘልቅና ከሌላው ትምህርትና መግለጫ ጋር ስለቅጾች አሞላልና አመዘጋገብ በልኡካኑ አማካይነት ትምህርታዊ መግለጫ እንዲሰጥ በመደረጉ የስምሪት አንድና ሁለት ተልእኮ ከነውን በወቅቱ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለመሆን በቅቶአል ።

ከዚሁ ጋር በጉልህ የሚታየው ከአጠቃላይ ጉባኤ ምሥረታ በኋላ በተካሄደው የስምሪት አንድና ሁለት ተልእኮ ሰበካ ጉባኤን ከማደራጀት ጋር ትምህርተ ወንጌል ለምእመናን በስፋት እንዲሰጥ በመደረጉ ምእመናን በተስፋ እንዲጽናኑ ሆኖአል ።

ልኡካኑ በየተሰማሩባቸው ስፍራዎችና አካባ



www.ethiopianorthodox.org

ቢዎች በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ተልእኮ አፈጻጸም በኩል የተገነዘቡትን ያህል በመመዝገብ ካቀረቡአቸው ሪፖርቶችና እንዲሁም በየሰበካ ጉባኤያት ተመዝግበው ከተላኩት ቅጾች ሁለተኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊነጋገርባቸው የሚችል ዓበይት ነጥቦችን ለመቅረጽ የተቻለ ከመሆኑም በላይ የስምሪቱ ውጤት በሁሉም መንፈስ ውስጥ የፈጠረው አዲስ ስሜትና ስምሪቱ በየጊዜው እንዲቀጥል የሰጠው ግፊት ቀላል አልነበረም ።

፪ኛ/ <u>የስምሪት ሦስትና አራት ተልእኮ አፈጻጸም ፤</u>

ባለፈው ከታየው ተግባራዊ እንቅስቃሴና የእድገት ውጤት በመነሣት ሁለተኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ስምሪቱ እንዲቀጥል በሰጠው ውሳኔ መሠረት የስምሪት ሦስትና አራት ተልእኮ በወቅቱ እንዲቀጥል ተደረገ ።

በእነዚህ ተከታታይ የሥራ ስምሪቶች ባለፈው የታዩት ድክመቶች እንዲጠናከሩና የቅጾች አመዘጋገብ ጥራት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ።

ስለሆነም ለሁለተኛ ጊዜ የታተሙት ቅጾች ከፊተኛው በተሻለ ሁኔታ ግልጽና የተሟሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥናት ከተደረገ በኋላ የሰውንና የገንዘብ ኃይልን እንዲሁም የገቢንና የወጭን አሐዛዊ ድምር በግልጽ የሚያሳዩ ቅጾች በየደረጃው ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደረገ ።


ቀጥሎም በዚህ አንፃር የስምሪት ሦስትና አራት ተልእኮ የሥራ አፈጻጸምን በመቀየስ ወደየሀገረ ስብከቱ የሚሰማሩትን ልኡካን በመምረጥና ለልኡካኑ ጥናታዊ ጉባኤ በማዘጋጀት ፤ እንዲሁም ወቅቱንና እድገቱን የጠበቀ የሥራ መመሪያ በመስጠት ዝግጅቱ ተሟልቶ ስምሪቱ ተካሂዷል ።

፫ኛ/ <u>የስምሪት ፭ እና ፮ ተልእኮ አፈጻጸም ፤</u>

የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በአራቱ የሥራ ስምሪቶች የተፈጸሙትንና ያልተፈጸሙትን በመገምገም በውጥን ያሉትን ለማስፈጸምና ውጤቶችን ለማብዛት ፤ የእድገት ጉዳናዎችንም ለማስተካከል ቅጾችን ለሦስተኛ ጊዜ አሻሽሎ አሳትሞ ለየሀገረ ስብከቱ እንዲሰራጩ በማድረግ የስምሪት ፭ ተልእኮ ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ እንዲካሄድ አድርጓል ።

የስምሪቱ ልኡካንም ወቅቱና ከጊዜው ጋር የተገናዘበ የሥራ መመሪያ ይዘው ወደ የአህጉረ ስብከቱ ተሰማርተዋል ።

ልኡካኑ በየተሠማሩበተ ክፍል



የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከምርጫ በኋላ

— ስለስብከተ ወንጌል መስፋፋትና ስለሰበካ ጉባኤ መጠናከር
— ስለሰንበት ት/ቤቶች መቋቋም
— ስለጋዜጦችና መጽሔቶች ስርጭት
— ስለቅርሳቅርስ አጠባበቅ
— ስለልማት ሥራዎች
— በድርቅ ስለተጎዱ ወገኖች ርዳታ - - - የተቻለው ሁሉ ጥረት እንዲደረግ ትምህርታዊ ጉባኤ ከማካሄዳቸው ሌላ በየአብያተ ክርስቲያናቱ በዕለተ ሰንበትና በተለያዩ ዓበይት በዓላት ለምእመናን መንፈሳዊ ትምህርትን በማበርከት ሐዋርያዊ ተልእኮ አከናውነዋል ።

በተለይም እስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ የተመዘገቡትንና ያልተመዘገቡትን ምእመናን የሚያጠቃልል ቅጽ እንዲዘጋጅ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ቅጹ ተዘጋጅቶና ታትሞ በልኡካኑ አማካይነት ለየሀገረ ስብከቱ ተልኮ ስለነበር በዚህ ስምሪት መልስ አጥጋቢ እስታቲስቲካዊ መረጃዎች ተጠናክረው ቀርበዋል።

ልኡካኑም ከአጥቢያ እስከ ሀገረ ስብከት በየደረጃው ተሠርተው የቀረቡትን ቅጾችና የየሀገረ ስብከቱን ጠቅላላ ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በመገምገም ትምህርታዊ መመሪያ ሰጥተው ተመልሰዋል ።

ከዚህም ሌላ በአንዳንድ ሀገረ ስብከት ልዩ ሰሚናር (የጥናት ጉባኤ) ማድረግአስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤


ሀ/ በኤርትራ ሀገረ ስብከት ከመጋቢት ፳ እስከ ፳፭ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም

ለ/ በአርሲ ሀገረ ስብከት ከየካቲት ፱ ቀን እስከ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም

ሐ/ በአርሲ ሀገረ ስብከት ከየካቲት ፫ ቀን እስከ የካቲት ፭ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ/ም በከፍተኛ ደረጃ የሥራ ስምሪትቶችና ትምህርታዊ ጉባኤዎች ተካሂደዋል ።




<u>1975 ዓ. ም. — 1978 ዓ. ም. በየዓመቱ ሰበካ ጉባኤ የተቋቋመባቸውን ሰንበት ትምህርት ቤት ያላቸውን አብያተ ክርስቲያናት ብዛት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ።</u>





www.ethiopianorthodox.org

1976 ዓ.ም. — 1978 ዓ.ም. በሰበካ ጉባኤ በየዓመቱ የተመዘገቡትን ቋሚ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት መምህራን ብዛት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ።





በሰበካ ጉባኤ በየዓመቱ የተመዘገቡ ፡ በግንባር የሚያገለግሉ ካህናትና ልዩልዩ ሠራተኞችን ብዛት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ።





www.ethiopianorthodox.org

## 1975 ዓ. ም. — 1978 ዓ. ም. በየዓመቱ በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡትን ምእመናን ብዛት ሀ/ በጠ.ስ

### ለ/ ከነቤተ ሰቦቻቸው ጭምር የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ።




## ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ በየደረጃው የተቋቋሙት ሰበካ ጉባኤያት በየዓመቱ የሚያገኙትን ገቢ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ። 1975 ዓ. ም. —1978 ዓ. ም.




www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፭

# ሰበካ ጉባኤን ለማደራጀትና ለማጠናከር በየሥራ ዘርፉ በተደረገው ጥረት የተገኘ

## አጠቃላይ ውጤት ፤

ለቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳደር ተሐድሶ መሠረት የሆነው የተሻሻለው የቃለ ዋዓዲ ደንብ ከወጣ ወዲህ በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እስከ መንበረ ፓትርያርኩ ድረስ በየደረጃው የሰበካ ጉባኤ ተቋቁሞ ከመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ሁሉም በየበኩሉ የራሱን ድርሻ ለመፈጸም በሚያደርገው ጥረት የተገኘው ውጤት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ፤ ከእኛ አልፎ ተርፎ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤም ከፍተኛ ግምት የተሰጠው እድገት እየታየ ነው ።

ይህንም በአጭሩ እንደሚከተለው መዘርዘር ይቻላል ።

፩ኛ/ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሰበካ ጉባኤ ከተቋቋመ ወዲህ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት ደመወዝ በመመደብ ረገድ ከፍተኛ እድገት ታይቷል ።

፪ኛ/ በሰበካ ጉባኤ ጥረት ካህናት ወደ የማእልጠኛው እንዲላኩና ስልጥነው የተመለሱትም ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲያበረክቱ እየተደረገ ነው ።

፫ኛ/ ምእመናን ከቤተክርስቲያን ማግኘት የሚገባቸውን መንፈሳዊ አገልግሎትና ራሳቸውም ለቤተ ክርስቲያን መፈጸም የሚገባቸውን መንፈሳዊ ግዴታ በበለጠ በመረዳት በየሰበካ ጉባኤው አማካይነት ለቤተ እግዚአብሔር የሚገባውን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያሳዩት በጎ ፈቃድና ትጋት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

፬ኛ/ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ማዕከላዊ አሠራርን ለማስፈን በሰበካ ጉባኤ መዋቅራዊ ይዘት የተዘረጋው አመራር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ነው ።

፭ኛ/ የገንዘብ ብኩንነት እንዳይኖር ለቁጥጥር የሚያመቹ ሞዴሎች ካርኔዎችና የሂሣብ መዛግብት በአዲስ መልክ ተዘጋጅተውና ታትመው ለየሀገረ ስብከቱ በመሰራጨታቸው በገንዘብ ገቢና ወጪ አሠራር ረገድ ከፍተኛ ለውጥ ተደርጎአል ፤ አጥጋቢ ውጤትም ታይቷል ።

፮ኛ/ የስብከተ ወንጌል መስፋፋትንና መጠናከርን በሚመለከት ከሰበካ ጉባኤ ገቢ ሰባኪያንን በደመወዝ በመመደብና ትምህርተ ወንጌል ለሁሉም እንዲዳረስ ለማድረግ በየአህጉረ ስብከቱ የሚታየው ሐዋርያዊ ተልእኮ እያደገ መጥቷል ።

፯ኛ/ የሰንበት ት/ቤትን በሚመለከት ውሉደ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ ትምህርት ለማነጽ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሰንበት ትምህርት ቤት ተቋቁሟል።

፰ኛ/ በአንዳንድ አጥቢያ ሰበካ ጉባኤያት ንኡሳን የልማት ሥራዎች በሚያበረታታ ሁኔታ እየተካሄዱ ነው ።

፱ኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ጉባኤ ላይ በሰጡት መመሪያ መሠረት ለመደበኛው መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መምህራን ከሰበካ ጉባኤ ገቢ በአንደኛ ደረጃ የወር ደመወዝ እንዲከፈልና ለተማሪዎቻቸውም በአንድ አንድ ቦታ የልብስና ምግብ ድጎማ እየተደረገ ስለሆነ ት/ ቤቶቹ በመጠናከር ላይ ይገኛሉ ።

፲ኛ/ በሰበካ ጉባኤያት አማካይነት በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳትና ጥንታውያን ቅርሶች የአቀማመጥና አጠባበቅ ሁኔታ ዘመናዊ መልክ እንዲኖረው እየተደረገ ነው ።

፲፩ኛ/ የጋዜጦችንና የመጽሔቶችን ስርጭት በሚመለከት ስብከተ ወንጌልን ማዳረስ የሚቻለው በቃል ብቻ ሳይሆን በጽሑፍም ጭምር ስለሆነ በመጠኑም ቢሆን ጋዜጦችና መጽሔትቶች ለየሀገረ ስብከቱ እየተላኩ ለምእመናን በመዳረስ ላይ ናቸው

ስለዚህ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተገለጹትውጤቶች በአብዛኛው በሰበካ ጉባኤ መቋቋምና መጠናከር የተገኙ መሆናቸውን ስንመለከት ሰበካ ጉባኤ ፍጹም ተስፋ የሚጣልበት የቤተ ክርስቲያናችን ዕድገትና ጥንካሬ መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል ።



## የወደፊት ዕቅዶች ፤

ከአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንሥቶ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ በየደረጃው በተዘረጋው የሰበካ ጉባኤ መዋቅር ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ የኃላፊነት ድርሻቸውን ለመወጣት በተናጠልም ሆነ በማኅበር ባደረጉት ተግባራዊ እንቅስቃሴ አያሌ እቅዶች በተግባር መተርጎማቸውና ብዙ ውጤቶችም መገኘታቸው ከፍብሎ በተገለጸው ዝርዝር ተመልክቶአል ።

ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ፣

፩ኛ/ አሁን ካሉን ፳ሺህ ያህል አብያተ ክርስቲያናትና ከ፳ ሚልዮን በላይ የሚሆኑ ምእመናን መካከል እስከ አሁን በሰበካ ጉባኤ የተደራጁት በቅጹ ላይ እንደሚታየው ፲፫ሺ፩፪፰፩ አብያተ ክርስቲያናትና ፲፪ ሚልዮን ፩፪፰፪ ሽህ ፪፪፵፬ ምእመናን ብቻ ስለሆኑ የቀሩትን በተፈላጊው ሁኔታ ለማደራጀት ፣

፪ኛ/ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አንዳንድ ካህናት ለሰበካ ጉባኤ መቋቋምና መጠናከር ያላቸው አመለካከት አሁንም ዝቅተኛ ስለሆነ በዓላማው በትክክል አምነው የየበኩላቸውን ጥረትና ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማሳወቅና ለማሳመን ፣

፫ኛ/ የሰንበት ት/ቤቶችን በተሟላ ሁኔታ ለማቋቋምና የተቋቋሙትንም በጥራት ለማካሄድ ፣

፬ኛ/ የስብከተ ወንጌልን ስርጭት በኮርስ በሰለጠኑ መምህራን በበቂ ሁኔታ ለማዳረስ ፤

፭ኛ/ ለሁሉም ቋሚ መንፈሳዊ ትምህርት መምህራን በሰበካ ጉባኤ ገቢ በቂ ደመወዝ ለመክፈልና ለተማሪዎቻቸውም አስፈላጊውን ድጎማ ለማድረግ ፣

፮ኛ/ ለቤተ ክርስቲያን ቅርሳቅርስና ንዋያተ ቅድሳት በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በቂ የአያያዝና የአጠባበቅ ጥንቃቄ ለማድረግ ፣

፯ኛ/ የጋዜጦችና የመጽሔቶች ኅትመትና ስርጭት ለሁሉም ሀገረ ስብከት ሊዳረስ በሚችልበት ሁኔታ ለማሳደግ ፣

፰ኛ/ የገቢና የወጪ ሂሣብ አያያዝ በሁሉም ቦታ በጥራት እንዲካሄድ ለማድረግ ፣

፱ኛ/ በሰበካ ጉባኤ ሥር የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የልማት ዘርፎች በጥናትና በዕቅድ ሊካሄዱ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸትና የራስ አገዝ የልማት ፕሮጀክቶችንም ለማስፋፋት ፣

፲ኛ ስለድርብ ታቦታትና የድርብ ታቦታት በዓላት አከባበር ጉዳይ ከዚህ ቀደም የተላለፈው ውሳኔ በተግባር የተተረጐመ ስላልሆነ ይህን ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ - - - አሁንም ገና የሁሉንም ትጋትና ጥረት ይጠይቃል ።

ስለዚህ ከአሁን ቀደም በተደረገው የቅርብ የሥራ ክትትል የተገኙት ውጤቶች አጥጋቢ እንደ መሆናቸው መጠን ወደፊትም ይህንን ዕቅድ ከመጨረሻው ግብ ለማድረስ ትምህርት ፣ ቅስቀሳ ፣ ትምህርታዊ ውይይት ፣ የሥራ ስምሪትና ግምገማ በየጊዜው ማድረግ አሁንም አስፈላጊ ይሆናል ።

## ማጠቃለያ ፤

ይህ እስከ አሁን የታተተው ዘገባ በአጭሩ የሚያመለክተው በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድና ወሳኔ እንደገና ተሻሽሎ በወጣው የቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት ለማዕከላዊ አሠራር መስፈን ዓይነተኛ ምክንያት የሆነው የሰበካ ጉባኤ መዋቅር በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘርግቶ ፣ አገር አቀፉ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተመሥርቶ ፣ ሁሉም አምኖበትና ተስማምቶበት በሚወጣ የሥራ መመሪያ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮ ለማከናወን የሚያስችል የአስተዳደር ተሐድሶ ከተደረገ ወዲህ በሁሉም አቅጣጫ የተገኘውን የእድገትና ጥንካሬ ደረጃ ነው ።

ይህም የማዕከላዊ አሠራርን ፍሬያማነትና የአንድነትን ኃይል አጉልቶ የሚያሳይ በመሆኑ ራስን በመቻል በኩል ከታሰበው የእድገት ደረጃ ለመድረስ ሰበካ ጉባኤን ከማጠናከር የተሻለ ሌላ አማራጭ መንገድ እንደሌለ የሚያረጋግጥ ነው ።

እጅግ በጣም አበረታች የሆነው ይህ ውጤት ሊገኝ የቻለውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ይህን ኃላፊነት ከተረከቡበት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጡት አመራር በቤተ ክርስቲያናችን እድገትና ጥንካሬ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት በሰበካ ጉባኤ ተደራጅተው ስለቤተ ክርስቲያናቸው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት አፈጻጸም ለመነጋገርና የየበኩላቸውንም አሳብ ለማቅረብ የሚችሉበት የሰበካ ጉባኤያት አስተዳደር መዋቅር በመዘርጋቱ ፣ የሁሉም ጾታ ምእመናን ተወካዮች በብጹዕ ወቅዱስ ፓትርያርካችን ሊቀ መንበርነት በሚመራው አጠቃላይ ሰበካ መን



www.ethiopianorthodox.org


ፈሳዊ ጉባኤ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ እየተገኙ በማዕ
በላዊ ደረጃ የሥራ እቅድና መመሪያ በኅብረት ለመ
ቀየስ በመብቃታቸው ፤ በሊቀ ማእምራን አበባው
ይግዛው የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራአስኪያጅ
ሊቀ መንበርነት የሚመራው የመንበረ ፓትርያርክ
አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
ውጤታማ የሆነ የሥራ አፈጻጸም እቅድና መመሪያ
እየወጣ በሥራ እንዲተረጐምበማድረጉ፣ የሰበካጉባኤ
ማደራጃ መምሪያ ለታቀደው ሥራ አፈጻጸም የሥራ
ጊዜ ብቻ ሳይወስነው ሌት ተቀን ተግቶ በመሥ
ራቱና በጠቅላላም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት
ጀምሮ በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙት የቤተ ክርስቲያ
ኒቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስለሥራው ቀና አፈ
ጻጸም የየበኩላቸውን ግዴታ ለመወጣት ልባዊ ጥረት
በማድረጋቸው እንደሆነ እሙን ነው ።


ስለዚህ እስከ አሁን ስለተገኘው መልካም
ውጤት ስብሐት ለእግዚአብሔር እንላለን ።

ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትና ከየሀገረ ስብከቱ ርእሰ ከተሞች በስተቀር በቃለ ዓዋዲው በተወሰነው መሠረት ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ደረጃ በደረጃ የተቋቋሙትን የሰበካ ጉባኤያት ገቢ ፥ ክፍያና ድርሻ ሒሳብ በፐርሰንት /በመቶኛ/ የሚያመለክት ሠንጠረዥ ።

| ተራ ቁጥር | ደረጃው | ገቢ | ክፍያ | ድርሻ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን | 100% | 10% | 90% |
| 2 | ወረዳ | 10% | 5% | 5% |
| 3 | አውራጃ | 5% | 2% | 3% |
| 4 | ሀገረ ስብከት | 2% | 0.5% | 1.5% |
| 5 | መንበረ ፓትርያርክ | 0.5% | | 0.5% |

በየደረጃው የተቋቋሙት ሰበካ ጉባኤያት የገንዘብ አስተዋፅኦ ድርሻን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ።




የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አቋም ስዕላዊ መግለጫ


www.ethiopianorthodox.org

## አዘጋጅ !

በመጽሔት መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበው ይህ የ፬ ዓመት የሥራ ውጤት መድበል ! በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ

በሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ታተመ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን




# ማኅበረ ምእመናንን ለማደራጀትና ለማጠናከር ተሻሽሎ የወጣ

# የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ

ቃለ ዓዋዲ-ትርጓሜው-የአዋጅ ነጋሪ ቃል ። ኢሳ፥ ፵፥ ፫-ሉቃ፥ ፫፥ ፬-፮። ዮሐንስ ፩፥ ፲፱-፳፫።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም።
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org